# ሒሳብ

## የተማሪ መጽሐፍ
## 2ኛ ክፍል


አዘጋጅ

ሰማኸኝ ፈጠነ

መለሰ ይርሳዉ

መላኩ ቢያዝን

ገምጋሚዎች

ሙስጠፋ ከድር

ሮዳስ ድሪባ

ገስጥ አሰፋ

ሌይ አውት እና ኢሉስትሬሽን ዲዛይን:-እንጦጦ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ (ግርማ ዳርጌ)

አስማምቶ ያዘጋጀዉ

ሻዉል ዘነበ



ኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
ትምህርት ቢሮ

# ምስጋና

ይህ መጽሐፍ በትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ ካርታ ምክረ ሐሳብ መሰረት በኢፌዲሪ ትምህርት ሚንስቴር ተዘጋጅተው የቀረቡትን የሥርዓተ ትምህርት መጽሐፍት ማዘጋጃ ሰነዶችን መነሻ በማድረግ በአዲስ አበባ ከተማ አስተደደር ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ በሲዳማ ብሔራዊ ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ የማስማማት ዝግጅት የተደረገበት ሲሆን የማስማማት ዝግጅቱና የሕትመት ወጪው በሲዳማ ብሔራዊ ክልል መንግስትና በኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፕሮግራም-ኢ/GEQIP-E/ ተሸፍኖአል፡፡

በመሆኑም መጽሐፉን የማስማማት ዝግጅት ተደርጎበት መጠቀም እንዲቻል ለፈቀደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ፣ የማስማማት ዝግጅቱን በገንዘብ፣ በሰው ሃይልና በማቴሪያል፣ ልምዳቸውንና ዕውቀታቸውን በማጋራት ለረዱ፣እንዲሁም ሌሎችም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለደገፉ አካላት፣ተቋማትና ግለሰቦች ሁሉ የሲዳማ ትምህርት ቢሮ ምስጋናውን ያቀርባል፡፡

©የቅጂ መብት.

የመጽሐፉ ህጋዊ የቅጂ ባለቤት የአዲስ አበባ አስተዳደርና የሲዳማ ብሔራዊ ክልል ትምህርት ቢሮዎች ናቸው፡፡

© 2014፣ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ድሞክራሳዊ ሪፓብልክ ትምህርት ሚኒስቴር፤ የቅጂ መብት ሙሉ የተከበረ ነው፡፡ ያለፈቃድ ማተም፣ ማባዛት፣ ባልተገባ መንገድ ማከማቸትና በሃርድ ኮፒም ሆነ በሶፍት ኮፒ ማሰረጨት እንዲሁም ላልተገባ ዓላማ መጠቀም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ድሞክራሳዊ ሪፓብልክ፤ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር 410/2004 ቅጂ መብት እና ጥበቃ ደንብ መሰረት ያስቀጣል፡፡

የመጀምሪያ እትም 2016 ዓ.ም
ሲዳማ/ ሃዋሳ

# ማዉጫ


ይዘት ገጽ

**ምዕራፍ አንድ** ........................................................................ 1

**ቁጥሮች እስከ 1,000**.................................................................... 1

1.1 የ100 ብዜቶች.......................................................................... 1

1.2 ቁጥሮች እስከ 1000.................................................................. 5

1.3 እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች የቤት ዋጋ ...................... 8

1.4 እስከ 1000 ያሉ ሙሉቁጥሮችን ማወዳደር እና በቅደም ተከተል ማስቀመጥ ........................................................... 13

የምዕራፍ አንድ ማጠቃለያ ................................................... 22

የምዕራፍ አንድ ማጠቃለያ መልመጃ.................................... 23

**ምዕራፍ ሁለት** ......................................................................27

**ባለ ሦስት ሆሄ ቁጥሮችን መደመርና መቀነስ**......................... 27

2.1 እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር .................... 27

2.2 እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መቀነስ....................... 39

2.3 መደመር እና መቀነስን የያዙ የቃላት ፕሮብሌሞችን መፍታት ........................................................................................ 43

የምዕራፍ ሁለት ማጠቃለያ ................................................. 47

**ምዕራፍ ሦስት** .......................................................................51

**እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማባዛት** ..............................51

3.1 እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን ክለሳ........................................ 51

3.2 እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን በ2 ማባዛት ............................... 53

3.3 እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን በ2 እና በ10 ማባዛት.............. 57

3.4 እስከ 100 ያሉ ሙሉቁጥሮችን በ 0 እና 1 ማባዛት ........ 60

3.5.እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን በ3፣4፣5፣6፣7፣8 እና በ9 ማባዛት ........................................................................................ 63

3.6 የቃላት ፕሮብሌሞች ........ 66
የምዕራፍ ሶስት ማጠቃለያ ........ 70
የምዕራፍ ሶስት ማጠቃለያ መልመጃ ........ 71

**ምዕራፍ አራት ........ 74**

**ግማሽ እና ሩብ ........ 74**
4.1 ግማሾች ........ 74
4.2 ሩቦች ........ 77
የምዕራፍ አራት ማጠቃለያ ........ 80
የምዕራፍ አራት ማጠቃለያ መልመጃ ........ 81

**ምዕራፍ አምስት ........ 83**

**ንድፎች ........ 83**

5.1 አሃዳዊ ድግግሞሽ ........ 83
5.2 የጎደሉ የንድፍ አባላቶች ........ 86
የምዕራፍ አምስት ማጠቃለያ ........ 88

**ምዕራፍ ስድስት ........ 91**

***ልኬት: ርዝመት፣መጠነቁስ እና ይዘት ........ 91***
6.1. ርዝመትን በሳንቲሜትር እና በሜትር መለካት ........ 91
6.2 ተመሳሳይ የርዝመት መለኪያ ምድብ ያላቸውን መደመርና መቀነስ ........ 95
6.3 መጠነ ቁስ በኪሎግራም እና በግራም መለካት ........ 98
6.4 ተመሳሳይ የመጠነ ቁስ መለኪያ ምድብ ያላቸውን መደመርና መቀነስ ........ 100
6.5 ይዘትን በሊትር እና በሚሊ ሊትር መለካት ........ 103
6.6 ተመሳሳይ የይዘት መለኪያ ምድብ ያላቸውን መደመርና መቀነስ ........ 105
የምዕራፍ ስድስት ማጠቃለያ ........ 108

የምዕራፍ ስድስት ማጠቃለያ መልመጃ ................................ 109

ምዕራፍ ሰባት ..........................................................111

መረጃ አያያዝ ............................................................ 111
7.1 መረጃ መሰብሰብ......................................................... 111
7.2 ከተሳለ ስዕል በመነሳት መረጃዎችን መመደብ................ 114
7.3 ቁሶችን በመጠቀም መረጃዎችን ማደራጀት .................... 118
የምዕራፍ ሰባት ማጠቃለያ .............................................. 121
የምዕራፍ ሰባት ማጠቃለያ መልመጃ .................................. 122

ምዕራፍ ስምንት ........................................................124

የጂኦሜትሪ ቅርፆች ......................................................... 124
8.1 የጠለል ምስሎችን በማየት መመደብ............................ 124
8.2 ቅርፆችን በጎናቸውና በኮርነራቸው መግለፅ..................... 126
8.3 ተመሳሳይ ምስሎችን በመጠናቸው ማወዳደር ................ 128
8.4 ጠጣር ምስሎችን መለየት .............................................. 131
የምዕራፍ ስምንት ማጠቃለያ............................................. 133
የምዕራፍ ስምንት ማጠቃለያ መልመጃ............................... 133

ምዕራፍ ዘጠኝ..........................................................135

የኢትዮጵያ ገንዘብ ........................................................... 135
9.1 የኢትዮጵያን ገንዘብ በመጠቀም መደመርና መቀነስ ........ 135
9.2 ግብይትን የሚሳይ ጭውውት........................................ 138
9.3 የቃላት መልመጃዎች ................................................... 140
የምዕራፍ ዘጠኝ ማጠቃለያ ............................................... 142
የምዕራፍ ዘጠኝ ማጠቃለያ መልመጃ.................................. 142

ምዕራፍ አስር...........................................................145

የኢትዮጵያ ጊዜ ............................................................... 145

10.1 ሰዓትን በሙሉ ፣በግማሽና በሩብ አቆጣጠር በዲጂታልና በሚዞር ሰዓት ...... 145
10.2 ሰዓትና ደቂቃ ...... 149
10.3 የጊዜ የቃላት መልመጃዎች መፍታት ...... 151
የምዕራፍ አስር ማጠቃለያ ...... 153
የምዕራፍ አስር ማጠቃለያ መልመጃ ...... 154

# ምዕራፍ አንድ

# ቁጥሮች እስከ 1000

*የምዕራፉ የመማር ውጤቶች፣ ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ በኋላ፣*

- *ቁሶችን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ ትረዳላችሁ።*
- *እስከ 1000 ያሉ ሙሉቁጥሮችን ማወዳደር በቅደም ተከተል ማስቀመጥ ትችላላችሁ።*

## 1.1 የ100 ብዜቶች

*ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት፡*

- *የ100 ብዜቶችን መቁጠር፣መፃፍ እና ማንበብ*

*ተግባር 1.1*

ሀ. 100፣ 300፣ 500 እና 800ን በክፍል ውስጥ በቃላችሁ አንብቡ።

ለ. 300፣ 500፣ 600፣ እና 700ን በ100 ብዜቶች ድምር ግለፁ ።

## አስተውሉ

✍ ማባዛት ማለት የመደመር ድግግሞሽ ነው፡፡

**ምሳሌ**

ሀ. $4 \times 100 =$ _____

መፍትሔ

$4 \times 100 = 100 + 100 + 100 + 100$

$= \mathbf{400}$ (አራት መቶ)

ስለዚህ 400 የመቶ ብዜት ነው፡፡

ለ. $5 \times 100 =$ ____________

መፍትሔ

$5 \times 100 = 100 + 100 + 100 + 100 + 100$


$= \mathbf{500}$ (አምስት መቶ)

ስለዚህ 500 የመቶ ብዜት ነው፡፡

## አስተውሉ

✍የመቶ ብዜት ቁጥሮች በሁለት ዜሮዎች የሚጨርሱ ናቸዉ።

✍የሚከተሉት ቁጥሮች የመቶ ብዜት ናቸው።




## መልመጃ 1.1

1. የ100 ብዜቶችን በጎደሉ ቦታዎች ላይ ሙሉ።

| × | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 100 | | | | | | | | | |

2. ቀጥሎ ያለፉትን ቁጥሮች በፊደል ጻፉ ፡፡

| በቁጥር | በፊደል |
|---|---|
| 100 | |
| 200 | |
| 300 | |
| 400 | |
| 500 | |
| 600 | |
| 700 | |
| 800 | |
| 900 | |

3. የአስቴር እናት የ100 ብር አፕል እና የ200 ብር ብርቱኳን ገዛች፡፡ በአጠቃላይ ስንት ብር ከፈለች?



4. ከሚከተሉት ቁጥሮች መካከል የመቶ ብዜት የሆኑትን ለዩ፡፡

50፣200፣500፣750፣600፣920፣900

5. የመጀመሪያዎቹን አምስት የመቶ ብዜቶች ጻፉ፡፡

## 1.2 ቁጥሮች እስከ 1000

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት፡

- *ቁጥሮችን ወደፊት መቁጠር፣ወደኋላ መቁጠር እና እየዘለሉ ማንበብ*
- *ቁጥሮችን በ100፣ በ10 እና በ1 ሰብስቦ ማስቀመጥ*

*ተግባር 1.2*

ሀ. የሚከተሉትን ቁጥሮች አንብቡ።

300፣410፣456፣546፣678፣589

ለ. የሚከተሉትን ቁጥሮች ወደ ፊት እና ወደ ኋላ አንብቡ።

221፣325፣456፣354፣474፣123፣222፣700

ሐ. የሚከተሉትን ቁጥሮች ከ125 በመጀመር ሶስት ቁጥሮችን፣ አራት ቁጥሮችንና ሰባት ቁጥሮችን እየዘለላችሁ አንብቡ።

125፣235፣342፣444፣523፣671፣780፣827፣937፣989

**ምሳሌ**

1. ከዚህ በታች ያሉትን ቁጥሮች በመመልከት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡

113፣120፣131፣236፣274፣357፣340፣437፣442፣517፣632፣751

ሀ. ከላይ ያሉትን ቁጥሮች ከ 113 ጀምረን በአንድ ቁጥር እየዘለልን ስናነብ

113፣131፣274፣340፣442፣632፣ ይሆናሉ።


ለ. ከላይ ያሉትን ቁጥሮች ከ 113 ጀምረን በሁለት ቀጥሮች እየዘለልን ስናነብ

113፣236፣340፣517፣800 ይሆናሉ።

ሐ. ከላይ ያሉትን ቁጥሮች ከ 120 ጀምረን በአራት ቀጥሮች እየዘለልን ስናነብ

120፣340፣751 ይሆናሉ።

2. 992ን በመቶ፣በአስር እና በአንድ ሰብስበን ስናስቀምጥ





9 መቶዎች 9 አስሮች 2 አንዶች

3. የ100 ብዜቶችን ለመቁጠር ቁሶችን በ 100 ምድቦች መመደብ

**ምሳሌ**

300ን በመቶ ምድቦች ስንመድብ



**መልመጃ 1.2**

1. ቀጥሎ ያሉትን ቁጥሮች በማየት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ስሩ፡፡

230፣255፣325፣368፣389፣456፣487፣547፣569፣589፣600፣612፣684፣672

ሀ. ከ230 በመጀመር በሁለት ቀጥሮች እየዘለላችሁ ጻፉ፡፡

ለ. ከ255 በመጀመር በአራት ቀጥሮች እየዘለላችሁ ጻፉ፡፡

ሐ. ከ368 በመጀመር በሰባት ቀጥሮች እየዘለላችሁ ጻፉ፡፡

2. የሚከተሉትን ቁጥሮች በ100፣ በ10 እና በ1 ሰብስባችሁ አስቀምጡ፡፡

ሀ.456 ለ.159

## 1.3 እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች የቤት ዋጋ

*ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት፡*

- *እስከ 1000 ያሉ የቁጥር ቤት ዋጋዎችን መረዳት*
- *የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የ1 ቤትን ፣የ10 ቤትን እና የ100 ቤትን መረዳት*

**የቡድን ስራ 1.1**



1. በቁጥር 759 ውስጥ የ 7፣ 5 እና የ9 የቁጥር ቤት ዋጋ ስንት እንደሆነ በቡድን ተወያዩበት፡፡
2. በቁጥር 168 ውስጥ የ1፣ 6 እና የ 8 የቁጥር ቤት ዋጋ ስንት ነው? በቡድን ተወያዩበት፡፡
3. ቀጥሎ ያሉትን ቁጥሮች አባከስን በመጠቀም የቁጥር ቤት ዋጋቸውን ፃፉ፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ. 13 | ለ. 612 |
| ሐ. 235 | መ. 947 |


**አስተዉሉ**

✍የቁጥር ቤት ዋጋ ስናስቀምጥ ከቀኝ ወደ ግራ የ1 ቤት፣የ10 ቤት እና የ 100 ቤት በማለት እናስቀምጣለን፡፡

**ምሳሌ 1.** 592 በቁጥር ቤት ዋጋ ሲቀመጥ

| የመቶ ቤት | የአስር ቤት | የአንድ ቤት |
|---|---|---|
| 5 | 9 | 2 |

1.456 በቁጥር ቤት ዋጋ ሲገለፅ





1.ከታች የተሰጠው አባከስ በቁጥር ቤት ተመስርቶ የተዘጋጀ ነው።

በአንድ ቤት ውስጥ 4 ጨሌዎች ፣ በአስር ቤት ውሰጥ 2 ጨሌዎች እና በመቶ ቤት ውስጥ 3 ጨሌዎች ተቀምጠዋል።


ስለዚህ 3 መቶዎች፣2 አስሮች እና 4 አንዶች አሉ።

324 = 300 + 20 + 4



2. 835 በቁጥር ቤት ዋጋ እንደሚከተለዉ ሊገለጽ ይችላል፡፡

8 መቶዎች + 3 አስሮች + 5 አንዶች



800 + 30 + 5=835



3. 485= -------- መቶዎች-------አስሮች እና -----------
አንዶች አሉት?

**መፍትሔ**

485፡- 4 መቶዎች፣8 አስሮች እና 5 አንዶች አሉት፡፡


4. 835 እና 690 በየቁጥር ቤት ዋጋቸዉ አስቀምጡ፡፡

**መፍትሔ**

| 835 | 690 |
|---|---|
|   |   |
| 8 3 5 | 6 9 0 |

### መልመጃ 1.3

1. የተሰጡትን ቁጥሮች በአባከሱ ላይ ጨሌዎችን በመጠቀም በቁጥር ቤት ግለፁ።



2. ቀጥሎ ያሉትን ቁጥሮች በቁጥር ቤታቸው ግለፁ፡፡

| ቁጥር | የመቶ ቤት | የአስር ቤት | የአንድ ቤት |
|---|---|---|---|
| 137 | | | |
| 216 | | | |
| 359 | | | |
| 461 | | | |
| 749 | | | |
| 837 | | | |
| 925 | | | |

3. ቀጥሎ ያሉትን ቁጥሮች የቁጥር ቤት ዋጋቸውን ግለፁ፡፡

ሀ. 210

ለ. 566

ሐ. 111


መ. 897

4. ከዚህ በታች ያሉት ቁጥሮች ስንት መቶዎች፣ አስሮች እና አንዶች እንዳሏቸው ግለፁ፡፡

ሀ. 427 = ____መቶዎች፣_____አስሮች እና_____ አንዶች

ለ. 567 =_____መቶዎች፣______ አስሮች እና_____አንዶች

5. ባዶ ቦታዉን ሙሉ።




## 1.4 እስከ 1000 ያሉ ሙሉቁጥሮችን ማወዳደር እና በቅደም ተከተል ማስቀመጥ

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት፡

- *ቁሶችን በቅደም ተከተል አስተካክሎ ማስቀመጥን መረዳት*
- *የቁጥር መስመር በመጠቀም እስከ 1000 ያሉ ሙሉቁጥሮችን ማወዳደር እና በቅደም ተከተል ማስቀመጥ*
- *እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን የይበልጣል፣ የያንሳል እና የእኩልነት ምልክቶች በመጠቀም ማወዳደር*
- *የመቶ ብዜቶችን በቁጥር መስመር ላይ ማመልከት*

**ተግባር 1.4**

ካርድ በማዘጋጀት ከ110 እስከ 120 ያሉ ቁጥሮች በእያንዳንዱ ካርድ ላይ ጻፉ፡፡

ሀ. ከጻፋችሁት ቁጥር መካከል ትልቁ ቁጥር ስንት ነዉ?


ለ. ከጻፋችሁት ቁጥር መካከል ትንሹ ቁጥር ስንት ነዉ?

ሐ. ከትንሹ ቁጥር በመጀመር በቅደም ተከተል አስቀምጡ፡፡

**አስተውሉ**

- ሙሉ ቁጥሮችን እርስ በርሳቸው ማወዳደር ይቻላል፡፡
- ቁሶችን በአባላት ብዛት እርስ በርሳቸው ማወዳደር ይቻላል፡፡
- በምናወዳድርበት ጊዜ ይበልጣል (>) ፣ ያንሳል (<) እና እኩል ይሆናል (=) ምልክቶችን እንጠቀማለን፡፡

**ምሳሌ**

| | |
|---|---|
| ሀ.  |  |
| $4 = 4$ | |
| ለ.  |  |
| $3 < 6$ | |
| ሐ. 50 >45 | መ. 345 < 457 |

**መልመጃ 1.4**

1. ቀጥሎ ያሉትን ቁጥሮች በማወዳደር የ“>” ፣ “<” ወይም የ “=” ምልክቶችን በባዶ ቦታ ላይ ሙሉ፡

| ቁጥር | ምልክቶች (> ፣< ፣=) | ቁጥር |
|---|---|---|
| 6 | | 1 |
| 5 | | 5 |
| 9 | | 2 |
| 7 | | 8 |

2. ቀጥሎ ያሉትን ቁጥሮች በማወዳደር የ“>” ፣ “<” ወይም የ “=” ምልክቶችን በባዶ ቦታ ላይ ሙሉ፡፡

ሀ. 24 _____ 33 ለ. 11_____10

ሐ. 75 _____ 75 መ. 98_____99

3. ቀጥሎ ያሉትን ቁጥሮች በማወዳደር የ“>” ፣ “<” ወይም የ “=” ምልክቶችን በሳጥኑ ላይ ሙሉ፡፡

ሀ. 354 ☐ 512 ለ. 223 ☐ 145


ሐ. 100 ☐ 652 መ. 465 ☐ 465

**አስተዉሉ**


✍ የቁጥር መስመር ቁጥሮችን በቅደም ተከተል የምንገልፅበት መስመር ነው፡፡

**ምሳሌ**

1. እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች በቁጥር መስመር ሲገለፅ




2. የመቶ ብዜቶች በቁጥር መስመር ሲገለፅ





**ምሳሌ**

1. ከ 40 እስከ 46 ያሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል አስቀምጡ፡፡


**መፍትሔ**

**40፣ 41፣42፣43፣44፣45፣46**

2. የሚከተሉትን ቁሶች በማየት በብዛታቸዉ ከትንሹ በመጀመር በቅደም ተከተል አስቀምጡ፡፡



መፍትሔ



3. ከዚህ በታች ያሉትን ባለ አንድ አሃዝ ቁጥሮች ከትንሽ ወደ ትልቅ በቅደም ተከተል ፃፉ፡፡

7፣6፣4፣2፣1፣3፣9

መፍትሔ

**1፣2፣3፣4፣6፣7፣9**

4. ከዚህ በታች ያሉትን ባለ ሁለት አሃዝ ቁጥሮች ከትልቅ ወደ ትንሽ በቅደም ተከተል ፃፉ፡፡

24፣15፣34፣78፣90፣18

መፍትሔ

**90፣78፣34፣24፣18፣15**

5. ከዚህ በታች ያሉትን ባለ ሶስት አሃዝ ቁጥሮች ከትንሽ ወደ ትልቅ በቅደም ተከተል ፃፉ፡፡

312፣124፣575፣269፣190፣734፣851

መፍትሔ

**124፣190፣269፣312፣575፣734፣851**

6. የሚቀጥለው ሠንጠረዥ ከተሞች ከአዲስ አበባ ያላቸዉን ርቀት ያሳያል፡፡

| ከተማ | ርቀት በኪሎ ሜትር |
|---|---|
| ሀዋሳ | 275 |
| አዳማ | 90 |
| ባህርዳር | 552 |
| መቀሌ | 931 |
| ጅግጅጋ | 619 |
| አሶሳ | 664 |

ሀ. የከተሞችን ርቀት ከትንሽ ወደ ትልቅ በቅደም ተከተል አስቀምጥ/ጪ፡፡

**መፍትሔ**

90፣ 275፣ 552፣ 619፣ 664፣ 931

ለ. ከተሞችን ከአዲስ አበባ ባላቸው ርቀት ከሩቅ ወደ ቅርብ በቅደም ተከተል ፃፉ፡፡

**መፍትሔ**

መቀሌ፣ አሶሳ፣ጅግጅጋ፣ባህር ዳር፣ ሃዋሳ፣አዳማ

## መልመጃ 1.5

1. የሚከተሉትን ባለ ሁለት አሃዝ ቁጥሮች በቅደም ተከተል ፃፉ።

   ሀ. ከ 22 እስከ 26

   ለ. ከ 38 እስከ 43

   ሐ. ከ72 እስከ 78

2. የሚከተሉትን ባለ ሶስት አሃዝ ቁጥሮች በቅደም ተከተል ፃፉ።

   ሀ. ከ313 እስከ 320

   ለ. ከ422 እስከ 429

   ሐ. ከ600 እስከ 610

3. የሚከተሉትን የተዘበራረቁ ቁጥሮች ከትንሽ ወደ ትልቅ በቅደም ተከተል ፃፉ።

   400፣445፣334፣320፣670፣712፣884፣937፣118፣192፣212

4. የሚከተሉትን የተዘበራረቁ ቁጥሮች ከትልቅ ወደ ትንሽ በቅደም ተከተል ፃፉ።

   30፣13፣28፣37፣56፣22፣92፣38፣79፣82፣73፣96

5. አቶ ሚኪያስ፣ወ/ሮ አልማዝ እና አቶ አብዲ ለአባይ ግድብ ከሰፈር 314፣412፣350፣500፣720፣560፣937፣830፣ 212፣ 437 ብር አሰባሰቡ። የተሰበሰበውን ብር ከትንሽ በመጀመር በቅደም ተከተል ፃፉ።

### የምዕራፍ አንድ ማጠቃለያ

- ማባዛት ማለት የመደመር ድግግሞሽ ነው።
- የመቶ ብዜት ቁጥሮች በሁለት ዜሮዎች የሚጨርሱ ናቸው።
- የቁጥር ቤት ዋጋ ስናስቀምጥ ከቀኝ ወደ ግራ የ1 ቤት፣የ10 ቤት እና የ 100 ቤት በማለት እናስቀምጣለን።
- ሙሉ ቁጥሮችን እርስ በርሳቸው ማወዳደር ይቻላል።
- ቁሶችን በአባላት ብዛት እርስ በርሳቸዉ ማወዳደር ይቻላል።
- በምናወዳድርበት ጊዜ ይበልጣል (>) ፣ ያንሳል (<) እና እኩል ይሆናል (=) ምልክቶችን እንጠቀማለን።
- የቁጥር መስመር ቁጥሮችን በቅደም ተከተል የምንገልፅበት መስመር ነው።

## የምዕራፍ አንድ ማጠቃለያ መልመጃ

☞ዓረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ እውነት ትክክል ካልሆነ ሀሰት በማለት መልሱ፡፡

1. አንድ መቶ ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር ነው፡፡
2. 530 የመቶ ብዜት ነው፡፡
3. 354 ከ 467 ያንሳል፡፡
4. 752 7 መቶዎች 5 አስሮች እና 2 አንዶች አሉት፡፡

☞ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡

1. ከሚከተሉት ውስጥ እዉነት የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. 75 < 62 ለ.320 > 210

   ሐ. 300 < 290 መ.199 > 400

2. ከሚከተሉት አንዱ የመቶ ብዜት አይደለም፡፡

   ሀ. 305 ለ.200

   ሐ. 700 መ.900

3. ከሚከተሉት ቁጥሮች መካከል ትልቁ ቁጥር የቱ ነው?

   ሀ. 564 ለ.247

   ሐ. 642 መ.700

4. በ 789 ውስጥ የመቶ ቤት የሆነው የቱ ነው?

   ሀ.8 ለ.7 ሐ.9 መ.89

☞የሚከተሉትን ጥያቄዎች በትዕዛዙ መሰረት መልሱ፡፡

1. እስከ 1000 ያሉ የ100 ብዜት ቁጥሮችን በሙሉ ፃፉ፡፡

2. የሚከተሉትን ቁጥሮች በማየት የ100 ብዜት የሆኑትን ብቻ ፃፉ፡፡

200፣ 350፣500፣70፣253፣590፣800፣870፣900፣540፣
400፣390፣10፣100፣340፣150፣600፣715

3. ባዶ ቦታውን ሙሉ፡፡

| ቁጥር | የመቶ ቤት | የአስር ቤት | የአንድ ቤት |
|---|---|---|---|
| 125 | | | |
| 222 | | | |
| 354 | | | |
| 751 | | | |
| 200 | | | |
| 991 | | | |

4. በሳጥኑ ውስጥ < ፣> እና = ምልክቶችን በማስገባት ዓረፍተ ነገሩን እውነት አድርጉ፡፡

ሀ.354 ☐ 124 ለ.543 ☐ 763

ሐ.777 ☐ 777 ሐ.961 ☐ 891

5. ቀጥሎ ያለው ሰንጠረዥ በአዲስ አበባ ከተማ ያሉ ክፍለ ከተሞች ያላቸውን ትምህርት ቤቶች ብዛት ያሳያል።

| ክፍለ ከተማ | ትምህርት ቤት ብዛት (የመንግስት) |
|---|---|
| ለሚ ኩራ | 33 |
| ልደታ | 35 |
| ቂርቆስ | 43 |
| ቦሌ | 37 |
| ንፋስ ስልክ ላፍቶ | 59 |
| አራዳ | 45 |
| አቃቂ ቃሊቲ | 76 |
| አዲስ ከተማ | 45 |
| ኮልፌ ቀራኒዮ | 61 |
| የካ | 64 |
| ጉለሌ | 48 |


ሀ. በቁጥር ብዙ ትምህርት ቤቶች ያለዉ ክፍለ ከተማ የቱ ነዉ?

ለ. በቁጥር ጥቂት ትምህርት ቤቶች ያለዉ ክፍለ ከተማ የቱ ነዉ?

ሐ. የትምህርት ቤቶችን ብዛት ከትልቁ ወደ ትንሹ በቅደም ተከተል አስቀምጡ፡፡

መ. ክፍለ ከተሞችን በትምህርት ቤቶች ብዛት ከትንሹ በመጀመር በቅደም ተከተል ፃፉ፡፡

6. ባዶ ታውን ሙሉ፡፡



# ምዕራፍ ሁለት

# ባለ ሦስት ሆሄ ቁጥሮችን መደመርና መቀነስ

*የምዕራፉ የመማር ውጤት፣ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ በኋላ*

- *እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር እና መቀነስን ትረዳላችሁ ።*

## 2.1 እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት፡

- *እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር*

**የቡድን ስራ2.1**



1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምሳሌው መሰረት ድምራቸዉን አግኙ።

| ↱ | +8 |
| --- | --- |
| 7 | 15 |
| 24 | |
| 9 | |
| 53 | |
| 234 | |

ሀ.

| ↱ | +324 |
| --- | --- |
| 27 | |
| 8 | |
| 123 | |
| 70 | |
| 675 | 999 |

ለ.


| ↱ | +13 |
| --- | --- |
| 29 | |
| 100 | |
| 8 | 21 |
| 457 | |
| 1 | |

ሐ.

2. የቁጥር ቤት ዋጋን በመጠቀም ደምሩ፡፡

ሀ. 15+24=__________ ለ.163+35=___________

3. ባዶ ቦታውን ሙሉ፡፡



4. የሚከተሉትን ቁጥሮች ቁልቁል ደምሩ፡፡

| ሀ. | ለ. | ሐ. | መ. |
|---|---|---|---|
| 324<br>+ 512<br>=_____ | 741<br>+ 235<br>=______ | 157<br>+ 632<br>=______ | 349<br>+ 294<br>=______ |

## 2.1.1 እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ያለ አለኝታ መደመር

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት፡


- *እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ያለ አለኝታ መደመር*

**አስተውሉ**

✍ ቁጥሮችን ቁልቁል ስንደምር ከቀኝ በመጀመር የአንድ ቤትን ከአንድ ቤት ጋር፣የአስር ቤትን ከአስር ቤት ጋር እና የመቶ ቤትን ከመቶ ቤት ጋር እንደምራለን፡፡

**ምሳሌ**

1. ባዶ ታውን ሙሉ፡፡




**መፍትሔ**

ስንደምር ከታች በመጀመር ወደ ላይ እንሄዳለን፡፡

0 +1=1፣ 1+2=3፣ 2 +3=5

በተመሳሳይ

1+3=4፣3+5=8 እና 4+8=12

2. የቁጥር ቤት ዋጋን በመጠቀም ደምሩ፡፡

ሀ. 25 +34

ለ. 157+ 432

ሀ. መፍትሔ

| | ቁጥር | የአስር ቤት | የአንድ ቤት |
|---|---|---|---|
| + | 25 | 2 | 5 |
| | 34 | 3 | 4 |
| | | 5 | 9 |
| =59 | | | |

ለ.

| | ቁጥር | የመቶ ቤት | የአስር ቤት | የአንድ ቤት |
|---|---|---|---|---|
| | 157 | 1 | 5 | 7 |
| + | 432 | 4 | 3 | 2 |
| | | 5 | 8 | 9 |
| =589 | | | | |

3. የሚከተሉትን ቁጥሮች ቁልቁል ደምሩ፡፡

| ሀ. | ለ. | ሐ. |
|---|---|---|
| 154<br>+ 810<br>= ____ | 544<br>+ 351<br>= ____ | 734<br>+ 61<br>= __ |

**መፍትሔ**

| ሀ. | ለ. | ሐ. |
|---|---|---|
| የአንድ ቤት | የአንድ ቤት | የአንድ ቤት |
| 4+0=4 | 4+1=5 | 4+1=5 |
| የአስር ቤት | የአስር ቤት | የአስር ቤት |
| 5+1=6 | 4+5=9 | 3+6=9 |
| የመቶ ቤት | የመቶ ቤት | የመቶ ቤት |
| 1+8=9 | 5+3=8 | 7+0=7 |
| =964 | =895 | =795 |

## መልመጃ 2.1ሀ

1.የሚከተሉትን ጥያቄዎች ድምራቸውን አግኙ፡፡

| | 200 | 134 | 561 | 320 | 502 |
|---|---|---|---|---|---|
| + 435 | | | | | |

2. የቁጥር ቤት ዋጋን በመጠቀም ደምሩ፡፡


ሀ. 61+17 ለ.125+231

ሐ.761+204 መ.452+47


3. የሚከተሉትን ቁጥሮች ቁልቁል ደምሩ፡፡

| ሀ. | ለ. | ሐ. | መ. |
|---|---|---|---|
| 257<br>+ 131<br>= ____ | 742<br>+ 123<br>= ____ | 321<br>+ 56<br>= ____ | 34<br>+ 61<br>= ____ |

4. ባዶ ቦታዉን ሙሉ።




ሀ.




ለ.

## 2.1.2 እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በአለኝታ መደመር

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት፡

- *እስከ 1000 ያሉ ሙሉቁጥሮችን በአለኝታ መደመር*

**ምሳሌ**

1. የቁጥር ቤት ዋጋን በተለያየ ዘዴ በመጠቀም መደመር።

ሀ. 27+38=______

**መፍትሔ**

| | |
|---|---|
| በቅድሚያ አንዶችን መደመር<br><br>7+ 8 = 15<br><br>1 አስር እና 5 አንዶች<br><br>ስለዚህ 5ን ፅፈን 1 አስር እናስቀራለን። | በመቀጠል አስሮችን እና ቀሪዎችን መደመር<br><br>1+2+3 = 6 |
| 1 አለኝ<br><br>27<br><br>+ 38<br><br>= _5 | 1<br><br>27<br><br>+ 38<br><br>= 65 |

ለ. 424 + 378 =

______

## መፍትሔ

| በቅድሚያ አንዶችን መደመር | በመቀጠል አስሮችን እና ቀሪዎችን መደመር | በመጨረሻም መቶዎችን እና ቀሪዎችን መደመር |
|---|---|---|
| 4+8 = 12<br>1 አስር እና 2 አንዶች<br>ስለዚህ 2ን ፅፈን 1 አስር እናስቀራለን:: | 2+7+1 =10<br>1 መቶ እና 0 አስሮች<br>ስለዚህ 0ን ፅፈን 1 መቶ እናስቀራለን:: | 4+3+1 = 8 |
| 1 አለኝ<br>424<br>+ 378<br>=__2 | 1<br>424<br>+ 378<br>=_02 | 1<br>424<br>+ 378<br>=802 |

ሐ. 178 + 47=______

## መፍትሔ

| የመቶ ቤት | የአስር ቤት | የአንድ ቤት | | |
|---|---|---|---|---|
| 1 | | | | |
| | 1 | | | 1+7+4=12 |
| 1 | 7 | 8 | 8+7=15 | |
| | 4 | 7 | | |
| 2 | 2 | 5 | | |

ስለዚህ 178 + 47=225

2. ባዶ ቦታውን ሙሉ፡፡

___

39 30

20 19 11

9 11 8 3

ስንደምር ከታች በመጀመር ወደ ላይ እንሄዳለን፡፡

በዚህም መሰረት

39 +30=69

**መልመጃ 2.1ለ**

1. የቁጥር ቤት ዋጋን በመጠቀም ደምሩ፡፡

ሀ. 35+89 =_________

ለ. 159+792 =_______


ሐ. 859+78 =_______

2. የሚከተሉትን ቁልቁል ደምሩ፡፡


| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | 15<br>+43<br>=___ | ለ | 125<br>+ 28<br>=___ | ሐ | 804<br>+149<br>=___ |

3. ባዶ ቦታውን ሙሉ፡፡

ሀ.




ለ.



## 2.2 እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መቀነስ

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት፡

- እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መቀነስ

**የቡድን ስራ 2.2**



1. ከታች ያሉትን 10 እየበረሩ ያሉ አውሮፕላኖች ተመልከቱ፡፡

አራቱ አውሮፕላኖች ቀድመው መሬት ላይ ቢያርፉ ስንት አውሮፕላኖች ይቀራሉ፡፡



2.



9ኳሶች

\-




7 ኳሶች

=____ኳሶች

3. 98 እስክርቢቶዎች - 71 እስክርቢቶዎች=__እስክርቢቶዎች

4. ባዶ ታውን ሙሉ፡፡



=__________

5. የሚከተሉትን ቁጥሮች ቁልቁል ቀንሱ።

| | | |
|---|---|---|
| 98<br>- 79<br>=______ | 120<br>-110<br>=______ | 398<br>- 99<br>=______ |

**አስተውሉ**

✍እያንዳንዱን ቁጥር ስንቀንስ በየቁጥር ቤት ዋጋው ነው።

## *2.2.1 በብድርና ያለ ብድር መቀነስ*

*ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት:*

- *ቁጥሮችን በብድርና ያለ ብድር መቀነስ*

**ምሳሌ**

1. የሚከተሉትን ቁጥሮች በየቁጥር ቤት ዋጋቸው ቀንስ/ሽ።

ሀ. 98- 72=___ ለ. 220 -110= __ ሐ. 398- 92= __

**መፍትሔ**

| ሀ | | | ለ | | | | ሐ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የ10 ቤት | የ1 ቤት | | የ100 ቤት | የ10 ቤት | የ1 ቤት | | የ100 ቤት | የ10 ቤት | የ1 ቤት |
| - | 9 | 8 | - | 2 | 2 | 0 | - | 3 | 9 | 8 |
| | 7 | 2 | | 1 | 1 | 0 | | | 9 | 2 |
| = | 2 | 6 | = | 1 | 1 | 0 | = | 3 | 0 | 6 |
| ስለዚህ 98- 72=26 | | | ስለዚህ 220 -110=110 | | | | ስለዚህ 398- 92=306 | | | |

2. የሚከተሉትን ቁጥሮች በየቁጥር ቤት ዋጋቸው በብድር ቀንሱ፡፡

657 – 429 = ?

| | | |
|---|---|---|
| ከ7 ላይ 9 መቀነስ ስለማይቻል ከ5 አስሮች 1 አስር እንበደራለን፡፡ 10 + 7 = 17 አንዶች ፡፡ አንዶችን ቀንሱ፡፡ ስለዚህ 17-9 =8 | በመቀጠል አስሮችን ቀንሱ፡፡ 4-2=2 | በመጨረሻም መቶዎችን ቀንሱ፡፡ 6-4=2 |

| 17 | 4 | |
|---|---|---|
| 657 | 657 | 657 |
| − 429 | − 429 | −429 |
| 8 | 28 | 228 |
| ስለዚህ 657-429= 228 | | |

## መልመጃ 2.2

1. የሚከተሉትን ቁጥሮች ቀንሱ።

| ሀ. | ለ. | ሐ. | መ. |
|---|---|---|---|
| 535 | 684 | 653 | 513 |
| − 202 | − 23 | − 271 | − 22 |
| =____ | =____ | =____ | =____ |

## 2.3 መደመር እና መቀነስን የያዙ የቃላት መልመጃዎችን መፍታት

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት፡

- በዕለት ተዕለት ህይወታቸው ወስጥ መደመር እና መቀነስን መተግበር

### የቡድን ስራ 2.3



1. አንድ የእንቁላል ነጋዴ ከገጠር 351 እንቁላሎችን ገዝቶ ወደ ቤት ሲገባ 35 እንቁላሎች መሰበራቸውን አየ፡፡ ከቀሩት ውስጥ 70ውን ቢሸጥ ስንት እንቁላሎች ቀሩት?ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩበት፡፡

2. አንድ ቀን ጠዋት አንድ ዳቦ ቤት 384 ዳቦዎችን ለመሸጥ አዘጋጅቶ 290 ብቻ ሸጠ፡፡

ያልተሸጡ ዳቦዎች ብዛት ስንት ነው?

3.ኅበሏ ተማሪ ከክፍል የላቀ ውጤት በማምጣቷ ትምህርት ቤቱ የ650 ብር መጻሕፍት ሸለማት፡፡ ኅበሏ ተማሪ ከተሸለመችው መፅሐፍ ዉስጥ የ250 ብሩን ለጓደኛዋ ሰጠቻት፡፡ ኅበሏ ተማሪ የስንት ብር መጻሕፍት ቀራት?



## አስተውሉ

ለቃላት መልመጃዎች መፍትሔ ሲፈለግ፡-

- *መጀመሪያ ጥያቄውን ደጋግሞ አንብቦ መረዳት፡፡*
- *ቀጥሎ የተሰጠውንና የሚፈለገውን መለየት፡፡*
- *በመጨረሻም መልሱን ማግኘት፡፡*

**ምሳሌ**

1.በቁም ሳጥኑ ውስጥ 4 ሱሪዎች፣6 ቲሸርቶችና 3 ሸሚዞች አሉ፡፡



ሀ. በቁም ሳጥኑ ውስጥ ያሉት ልብሶች ብዛት ስንት ነው?

ለ. የቲሸርቶች ብዛት ከሱሪዎች ብዛት በስንት ይበልጣል?

ሐ. የሸሚዞች ብዛት ከቲሸርቶች ብዛት በስንት ያንሳል?

## መፍትሔ

ሀ. በአጠቃላይ በቁም ሳጥኑ ውስጥ ያሉ ልብሶች ብዛት

=4+6+3

=13 ልብሶች

ለ 6 -4=2 2

ስለዚህ የቲሸርቶች ብዛት ከሱሪዎች በ2 ይበልጣል።

ሐ. 6-3=3

ስለዚህ የሸሚዞች ብዛት ከቲሸርቶች በ3 ያንሳል።

2. አንድ ትምህርት ቤት በመጀመሪያ አመት 536 ጠረጴዛዎችን ገዛ። በሚቀጥለው አመት ደግሞ 287 ቢገዛ በሁለቱ አመታት ውስጥ ስንት ጠረጴዛዎችን ገዛ?



**መፍትሔ**

ትምህርት ቤቱ የገዛቸው ጠረጴዛዎች ብዛት

= በመጀመሪያ አመት የተገዛው+ በሚቀጥለው አመት የተገዛው

=536+287

=823

3. ወ/ሮ ኤደን 850 ብር ይዘው ወደ ገበያ ሄዱ። በ130 ብር ለልጃቸዉ መፅሐፍ ገዝተው ተመለሱ። ወ/ሮ ኤደን ስንት ብር ቀራቸው?

**መፍትሔ**

ወ/ሮ ኤደን የቀራቸው ብር

= ወደ ገበያ ይዘው የሄዱት ብር - መፅሐፍ የገዙበት ብር

=850-130 =720

**መልመጃ 2.3**

1. የራሄል ወላጆች ለአንድ ትምህርት ቤት 60 የሒሳብ መፅሐፍና 50 የእንግሊዘኛ መፅሐፍ በስጦታ አበረከቱ። የራሄል ወላጆች በአጠቃላይ ለትምርት ቤቱ ስንት መፅሐፍ አበረከቱ?

2. በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ በአጠቃላይ 60 የ2ኛ ክፍል ተማሪዎች አሉ፡፡ 34ቱ ሴት ተማሪዎች ቢሆኑ በክፍሉ ውስጥ ስንት ወንድ ተማሪዎች አሉ?
3. ብርሃኑ 45 የእንቁላል ጣይ ዶሮዎች እና 15 በጎች ገዝቶ ያረባል፡፡ ብርሃኑ በድምሩ ስንት የቤት እንስሳት አሉት?
4. የአቤል እድሜ ከወንድሙ እድሜ በ4 ዓመት ያንሳል፡፡ የወንድሙ እድሜ አሁን 12 ዓመት ነዉ፡፡ የአቤል እድሜ ስንት ነው?

## *የምዕራፍ ሁለት ማጠቃለያ*

- ቁጥሮችን ቁልቁል ስንደምር ከቀኝ በመጀመር የአንድ ቤትን ከአንድ ቤት ጋር፣የአስር ቤትን ከአስር ቤት ጋር እና የመቶ ቤትን ከመቶ ቤት ጋር እንደምራለን፡፡
- እያንዳንዱን ቁጥር ስንቀንስ በየቁጥር ቤት ዋጋው ነው፡፡
- ለቃላት መልመጃዎች መፍትሔ ሲፈለግ፡- መጀመሪያ ጥያቄውን ደጋግሞ አንብቦ መረዳት፣ቀጥሎ የተሰጠውንና የሚፈለገዉን መለየት፣በመጨረሻም መልሱን ማግኘት፡፡
- ባለ 2 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ 3 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ጋር ያለ አለኝታና በአለኝታ መደመር ይቻላል፡፡
- ባለ 2 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ 3 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ጋር ያለ ብድርና በብድር መቀነስ ይቻላል፡፡

## የምዕራፍ ሁለት ማጠቃለያ መልመጃ

✍ ዓረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ እውነት ትክክል ካልሆነ ሀሰት በማለት መልሱ።

1. ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮችን ከባለ ሶስት ሆሄ ቁጥሮች ጋር መደመር ይቻላል።
2. ቁጥሮችን ስንደምርም ሆነ ስንቀንስ የቁጥር ቤት ዋጋን እንጠቀማለን።
3. ቁጥሮችን ስንቀንስ ከቀኝ በመጀመር ነው።

✍ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።

1. 345 + 23 =______

ሀ. 575 ለ. 368 ሐ. 548 መ. 322

2. 568 + 213 =______

ሀ. 355 ለ. 761 ሐ. 781 መ. 661

3. 468 — 351 =______

ሀ. 819 ለ. 217 ሐ. 710 መ. 117

4. 781 — 659 =______

ሀ. 122 ለ. 920 ሐ. 120 መ. 459

5. አብደላ 56 ብር አለው፡፡ 134 ብር አባቱ እና 54 ብር እህቱ ጨመሩለት፡፡ በአጠቃላይ አብደላ ስንት ብር አለው?

ሀ. 188 ለ. 110 ሐ. 244 መ. 190

✍ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በትዕዛዙ መሰረት መልሱ፡፡

1. ደምሩ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ. 178<br>+221<br>=___ | ለ. 516<br>+ 427<br>=___ | ሐ.331<br>+63<br>=___ | መ.444<br>+97<br>=___ |

2. ቀንሱ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ. 98<br>-47<br>=___ | ለ.494<br>-37<br>=_____ | ሐ. 274<br>- 138<br>=_____ | መ. 849<br>- 238<br>=___ |

3. የአቤነዘር ቤተሰቦች በግቢያቸው ውስጥ የከተማ ግብርናን በመጠቀም 12 የጥቅል ጎመን ችግኝ፣10 የቆስጣ ችግኝ እና 11 የሰላጣ ችግኝ አትክልቶችን ተከሉ፡፡ በአጠቃላይ የአቤነዘር ቤተሰቦች ስንት የአትክልት ችግኞችን ተከሉ?



2. ባለፈው ዓመት በትምህርት ቤት የወላጆች ቀን ሲከበር ተማሪዎች ከወላጆቻቸው ጋር በመሆን 342 ችግኞችን ተከሉ፡፡በዚህ አመት ደግሞ 560 ችግኞትችን ተከሉ፡፡ ከተተከሉት ችግኞች ውስጥ 105 ችግኞች አልፀደቁም፡፡ በሁለቱ አመታት ውስጥ ስንት ችግኞች ፀደቁ?



3. ተማሪዎች በዕረፍት ሰዓታቸው ከወላጆቻቸው ጋር በኢትዮጵያ ያሉ ታሪካዊ ቦታዎችን ለመጎብኘት ሄዱ፡፡ከነዚህ ተማሪዎች ውስጥ 246ቱ ላሊበላን፣ 204ቱ አክሱምን እና 215ቱ ሶፍኡመር ዋሻን ጎበኙ፡፡በአጠቃላይ ወደ ጉብኝት የሄዱ ተማሪዎች ብዛት ስንት ነው?





# ምዕራፍ ሦስት

# እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማባዛት

## 3.1 እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን ክለሳ

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት፡

- *እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን መከለስ*

**የቡድን ስራ 3.1**



1. ያልተሟሉ ቁጥሮችን ፃፉ።




2. ባዶ ታውን ሙሉ።

ሀ.10፣15፣20፣_፣ _፣ _፣ _ 45

ለ. 10፣ 20፣ 30፣ _፣_፣_፣_80

ሐ.78፣77፣_ 75፣_ ፣_ ፣_

መ.99፣96፣93፣_፣87፣_፣_

3. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን በቡድን ሆናችሁ ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩባቸው።

ሀ. ትልቁ ባለ አንድ ሆሄ ቁጥር ስንት ነው?

ለ. ትልቁ ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር ስንት ነው?

ሐ. ትልቁ ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር ሲቀነስ ትንሹ ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር ስንት ነው?

## መልመጃ 3.1

1. ከታች የተሰጡትን ቁጥሮች በቅደም ተከተል ዘርዝሩ።

ሀ.ከ16 እስከ 23

ለ.ከ81 እስከ 95

ሐ.ከ63 እስከ 72

መ.ከ8 እስከ 17

2. ባዶ ቦታውን ሙሉ።

ሀ.5፣10፣15፣_፣ _፣ _፣ _ 40

ለ. 90፣ 80፣ 70፣ _፣_፣_፣_20

ሐ.67፣68፣_70፣_፣_፣_

መ.50፣47፣44፣_፣38፣_፣_

## 3.2 እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን በ2 ማባዛት

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት፡

- *እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን በ2 ማባዛትን መረዳት*

የቡድን ስራ 3.2





1. በእያንዳዱ ሳጥን ውስጥ የሚገኙትን አፕሎች እና ኳሶች በመቁጠር የማባዛት ውጤቱን በባዶ ቦታው ላይ ሙሉ፡

ሀ.

|  |  |
|---|---|
| 2 | 2 |
| 2×2=__ | |

ለ.

|  |  |
|---|---|
| 3 | 3 |
| 3×2=__ | |

ሐ.

|  |  |
|---|---|
| 12 | 12 |
| 12×2=__ | |

2. በምሳሌው መሰረት ማባዛቱን በመደመር ግለፁ፡፡

ሀ. $3\times2=$ 3+3 ሐ. $13\times2=$ ____

ለ. $5\times2=$ ____ መ. $16\times2=$ ____


## አስተውሉ

- ቁጥሮችን በሁለት ማባዛት ማለት እጥፍ ማድረግ ነው፡፡
- ማባዛትን በመደመር መግለፅ እንችላለን፡፡



**ምሳሌ**

1. በእያንዳንዱ ሳጥን ውስጥ የሚገኙትን ሳይክሎች እና ቢራቢሮዎች በመቁጠር የማባዛት ውጤቱን በባዶ ቦታው ላይ ሙሉ፡፡

**ሀ.**

| | | |
|---|---|---|
|  |  |  |
| 3 | 3 | 6 |
| $3\times 2 =$ 3+3 =6 | | |

ለ.

| | | |
|---|---|---|
|  |  |  |
| 10 | 10 | 20 |
| $10\times 2 = 10+10=20$ | | |

2. በማባዛት የተቀመጡትን በመደመር ግለፁ፡፡

ሀ.$9\times2=$ ___  ለ.$13\times2=$ ___

**መፍትሔ**

ሀ.$9\times 2 = 9+9 =18$  ለ.$13\times 2 = 13+13 =26$

3. የ11 እጥፍ ስንት ነው፡፡

**መፍትሔ**

የ11 እጥፍ ማለት 11ን በ2 ማባዛት ማለት ነዉ፡፡

$11\times 2 = 11+11 =22$

## መልመጃ 3.2

1. የሚከተሉትን ቁጥሮች አባዙ።

   ሀ. 6×2= ___ ለ. 10×2= ___

   ሐ. 16×2= ___ መ. 19×2= ___

2. በማባዛት የተቀመጡትን በመደመር ግለፁ።


   ሀ. 7×2= __ ለ. 14×2= ___

   ሐ. 17×2= ___ መ. 20×2= ___

3. የሚከተለውን ሰንጠረዥ አሟሉ።

| × | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2 | | | | | | | | | |

4. መደመሩን በማባዛት ግለፁ።

| | |
|---|---|
|  |  |
| 18 | + 18 |
| ___________ | |

## 3.3 እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን በ2 እና በ10 ማባዛት


ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት፡

- *እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ2 እና በ10 ማባዛትን መረዳት*



**ተግባር 3.1**

1. የሚከተሉትን ምስሎች በመመልከት ባዶ ቦታውን ሙሉ።

ሀ.

| | |
|---|---|
|  |  |
| 4 | 4 |
| 4× _ = 8 | |

ለ.

| | |
|---|---|
|  |  |
| 10 | 10 |
| 2× 10 = _ | |

## አስተዉሉ

✍በአስር የተባዙ ቁጥሮች መጨረሻቸው ዜሮ ነው። ✍የቁጥር

ምሳሌ

ሀ. □ × 10 =400 ለ. □ × 10 = 180

ሐ. □ × 2 =188


**መፍትሔ**

ሀ. 40 × 10 =400 ለ.18×


10 =180

ሐ. 94 × 2 =188

2. እስከ 10 ያሉ የሁለት ብዜቶችን በ2 እየዘለልን በቁጥር መስመር ስናስቀምጥ



3. እስከ 100 ያሉ የአስር ብዜቶችን በ10 እየዘለልን በቁጥር መስመር ስናስቀምጥ




**መልመጃ 3.3**

1. ሳጥኑን የሚወክሉ ሙሉ ቁጥሮችን ፈልጉ፡፡

ሀ. ☐ × 2 =146 ለ. ☐ × 2 =192

ሐ. ☐ × 10 =540 መ. ☐ × 10 =670

2. ከ30 እስከ 40 ያሉትን የሁለት ብዜቶች በሁለት እየዘለላችሁ በቁጥር መስመር ላይ አመልክቱ፡፡

3. ከ40 እስከ 90 ያሉትን የአስር ብዜቶች በአስር እየዘለላችሁ በቁጥር መስመር ላይ አመልክቱ፡፡

## 3.4 እስከ 100 ያሉ ሙሉቁጥሮችን በ 0 እና 1 ማባዛት

*ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት፡*

- *እስከ 100 ያሉ ሙሉቁጥሮችን በ 0 እና በ1 ማባዛትን*



የቡድን ስራ

1. ምስሉን በማየት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

ሀ. ዜሮ በማባዛት ያለውን ልዩ ባህርይ ተወያዩበት፡፡

ለ. ማንኛውም ሙሉ ቁጥር በዜሮ ሲባዛ ውጤቱ ምን ይሆናል?



2. ከስዕሉ ምን ተረዳችሁ? ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩበት።




## አስተውሉ

- ✍ ማንኛዉም ቁጥር በ0 ሲባዛ ብዜቱ 0 ነው።
- ማንኛውም ቁጥር በ1 ሲባዛ ብዜቱ ራሱ ቁጥሩ ነው።

**ምሳሌ**

1. የዜሮ ብዜት በቁስ ሲገለፅ

| | | | |
|---|---|---|---|
|  ባዶ ቅርጫት |  ባዶ ቅርጫት |  ባዶ ቅርጫት |  ባዶ ቅርጫት |
| 0 | 0 | 0 | 0 |
| $0 + 0 + 0 + 0 = 4\times 0 = 0$ | | | |


2. የዜሮ ብዜት በቁጥር ሲገለፅ

ሀ. 0+0=2×0=0

ለ. 0+0+0=3×0=0

ሐ. 0+0+0+0=4×0=0

3. የአንድ ብዜት በቁሶች ሲገለፅ



የምትመለከቷቸው ቀይ ቀበሮዎች ናቸው። ብዛታቸው ደግሞ 4 ነው።

ስለዚህ 4×1 =4

4. የአንድ ብዜት በቁጥር ሲገለፅ

ሀ. 5× 1=5

ለ. 78×1=78

ሐ. 100×1=100

**መልመጃ 3.4**

ባዶ ቦታውን ሙሉ።

ሀ. 9× 0 =__

ለ. 44× 0 =__

ሐ. 21× 0 = __

መ. 7× 1 =__

ሠ. 99× 1 =__

ረ. 34× _ =34

## 3.5 እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን በ3፣4፣5፣6፣7፣8 እና በ9 ማባዛት

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት፡

- *ሙሉ ቁጥሮችን በ3፣4፣5፣6፣7፣8 እና በ9 ማባዛትን መረዳት*

**ተግባር 3.2**

የሚከተሉትን ቁጥሮች አባዙ፡፡




| | | |
|---|---|---|
| ሀ.7×3=__ | ለ.12× 4=__ | ሐ.18 × 5=__ |
| መ.50× 7=__ | ሠ.11 × 8=__ | ረ.27× 9=__ |

**አስተውሉ**







- ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥር ሲባዙ
  - ✓ መጀመሪያ የአንድ ቤት ሆሄ አባዝቶ የሚገኘዉን ብዜት በአንድ ቤት መፃፍ
  - ✓ ቀጥሎ የአስር ቤት ሆሄን አባዝቶ ብዜቱ ባለ አንድ ሆሄ ከሆነ በአስር ቤት፣ብዜቱ ባለ ሁለት ሆሄ ከሆነ ደግሞ በአስርና በመቶ ቤት መፃፍ
- ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ቁጥር ማባዛት እንችላለን፡፡

**ምሳሌ**

1. ማባዛትን በቁሶች ስናስቀምጥ

| | | |
|---|---|---|
|  |  |  |
| 6 | 6 | 6 |
| 6×3=6+6+6=18 | | |

2. የ4፣5፣6፣7፣8 እና የ9 ብዜቶች በተለያየ መንገድ ሲገለፁ

| የ4 ብዜት | የ5 ብዜት | የ6ብዜት |
|---|---|---|
|   |   |   |
| **የ7 ብዜት** | **የ8 ብዜት** | **የ9 ብዜት** |
|   |   |   |

3. 31ን በ3 ስናባዛ

| | |
|---|---|
| በቅድሚያ የአንድ ቤትን ማባዛትና ዉጤቱን በአንድ ቤት መፃፍ<br>3× 1 =3 | በመቀጠል የአስር ቤትን ማባዛትና ዉጤቱን በአስር ቤት መፃፍ<br>3× 3 =9 |
| 31<br>×3<br>3 | 31<br>×3<br>93 |
| 31× 3 =93 | |

4. 23ን በ4 ስናባዛ

| | |
|---|---|
| በቅድሚያ የአንድ ቤትን ማባዛትና ዉጤቱን በአንድ ቤት መፃፍ<br>4× 3 =12<br>አንድ አስርና 2 አንዶች ስለዚህ 2ን ፅፈን 1ን እናስቀራለን | በመቀጠል የአስር ቤትን ማባዛት 4× 2 =8 ከዚያም 8ን ከቀሪዉ ጋር መደመር<br>8+1 = 9 ዉጤቱን በአስር ቤት መፃፍ |
| 1 አለኝ<br>23<br>×4<br>_2 | 23<br>×4<br>92 |
| ስለዚህ 23× 4 =92 | |

## መልመጃ 3.5

1.የሚከተሉትን አባዙ፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ.13× 3=_____ | ለ.12× 5=_____ |
| ሐ.13× 8=_____ | መ.56× 4=_____ |
| ሠ.98× 6=_____ | ረ.84 × 7=_____ |
| ሰ.11× 9=_____ | ሸ.24× 8=_____ |

## 3.6 የቃላት ፕሮብሌሞች

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት፡

- *እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በዕለት ተዕለት ህይወታቸው ውስጥ በቃላት ፕሮብሌሞች ማባዛትን መተግበር*

**የቡድን ስራ 3.4**



1. ከ1ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች የመፅሐፍ ሽልማት ተዘጋጀ፡፡ በእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ የሚሸለሙ ተማሪዎች ብዛት አራት ቢሆኑ ስንት የሽልማት መፅሐፍት ያስፈልጋሉ?
2. በአንድ ትምህርት ቤት መማሪያ ክፍል ውስጥ 20 ዴስኮች ይገኛሉ፡፡ በእያንዳንዱ ዴስክ ላይ ሁለት ተማሪዎች ቢቀመጡ በአጠቃላይ በክፍሉ ውስጥ ስንት ተማሪዎች ይገኛሉ?

**ምሳሌ**

1. በአንድ ክፍል ውስጥ 4 ቡድኖች አሉ። በእያንዳንዱ ቡድን ዉስጥ 5 ተማሪዎች ቢኖሩ በአጠቃላይ በክፍሉ ዉስጥ ስንት ተማሪዎች አሉ?

**መፍትሔ**

ቡድኖቹ አምስት አምስት ተማሪዎች ስለሚይዙ

=5 + 5 + 5 + 5

= 4×5

=20

2. በአንድ ትምህርት ቤት ዉስጥ የሚገኙ ተማሪዎች የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ ከኮሮና ቫይረስ ለመጠበቅ 12 የእጅ መታጠቢያዎችን በ6 የተለያዩ ቦታዎች ላይ ቢያስቀምጡ በአጠቃላይ በትምህርት ቤቱ ዉስጥ ስንት የእጅ መታጠቢያዎች ይገኛሉ?



**መፍትሔ**

12 የእጅ መታጠቢያዎች በ6 የተለያዩ ቦታዎች

12+12+12+12+12+12

=12 x 6

=72

3. በአንድ የመኪና መሸጫ ዉስጥ 36 የቤት መኪናዎች አሉ። የእያንዳንዳቸዉ መኪኖች የእግር ጎማ ብዛት 4 ቢሆን በአጠቃላይ የመኪናዎች የእግር ጎማ ብዛት ስንት ነዉ?



**መፍትሔ**

እያንዳንዱ የቤት መኪና 4 ጎማዎች ስላሉት

36+36+36+36

$=4\times36$

$=144$

**መልመጃ 3.6**

1. ወ/ሮ አሚና 4 ተማሪ ልጆች አሏት። እያንዳንዳቸዉ ስምንት የመማሪያ ደብተሮች ያስፈልጋቸዋል። ወ/ሮ አሚና በአጠቃላይ ስንት ደብተሮች ያስፈልጓቸዋል?
2. አንድ ባለ ሱቅ በአንድ ቀን 9 ኪሎ ግራም ስኳር ሸጠ። የአንዱ ኪሎ ግራም ስኳር ዋጋ 28 ብር ቢሆን በአጠቃላይ ባለ ሱቁ በአንድ ቀን ስንት ብር ሸጠ?



3. አቶ ሄኖክ 7 የፓፓያ ችግኝ መደቦች አሉት። በእያንዳንዱ መደብ 43 የፓፓያ ችግኞች ተከለ። አቶ ሄኖክ በአጠቃላይ ስንት የፓፓያ ችግኞች ተከለ?



4. በአንድ ትምህርት ቤት የሚገኙ 40 የሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ከወላጆቻቸዉ ጋር በመወያየት ለተቸገሩ አረጋዉያን ለመደገፍ አምስት አምስት ብር አዋጡ። አረጋዉያንን ለመደገፍ ተማሪዎች በአጠቃላይ ስንት ብር አዋጡ?

## የምዕራፍ ሶስት ማጠቃለያ

- ቁጥሮችን በሁለት ማባዛት ማለት እጥፍ ማድረግ ነዉ፡፡
- ማባዛትን በመደመር መግለፅ እንችላለን፡፡
- በአስር የተባዙ ቁትሮች መጨረሻቸዉ ዜሮ ነዉ፡፡
- የቁጥር መስመርን በመጠቀም ከ0 ጀምረን በ2 እየዘለልን ስንቆጥር የ2 ብዜቶችን እናገኛለን፡፡
- የቁጥር መስመርን በመጠቀም ከ0 ጀምረን በ10 እየዘለልን ስንቆጥር የ10 ብዜቶችን እናገኛለን፡፡
- ማንኛዉም ቁጥር በ0 ሲባዛ ብዜቱ 0 ነዉ፡፡
- ማንኛዉም ቁጥር በ1 ሲባዛ ብዜቱ ራሱ ቁጥሩ ነዉ፡፡
- ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንደ ሙሉ ቁጥሮች ስናባዛ  መጀመሪያ የአንድ ቤት ሆሄን አባዝቶ የሚገኘዉን ብዜት በአንድ ቤት መፃፍ፣ቀጥሎ የአስር ቤት ሆሄን አባዝቶ ብዜቱን በአስርና በመቶ ቤት መፃፍ ይገባናል፡፡
- ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ቁጥር ማባዛት እንችላለን፡፡

## የምዕራፍ ሶስት ማጠቃለያ መልመጃ

☞ዓረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ እዉነት ትክክል ካልሆነ ሀሰት በማለት መልሱ፡፡

1. ማንኛዉም ቁጥር በ0 ሲባዛ ብዜቱ 0 ይሆናል ፡፡
2. ማንኛዉም ቁጥር በ1 ሲባዛ ብዜቱ ራሱ ቁጥሩ ይሆናል፡፡
3. ቁጥሮችን በ2 ማባዛት እና እጥፍ ማድረግ እኩል ናቸዉ፡፡
4. ማንኛዉም ቁጥር የ10 ብዜት ሊሆን ይችላል፡፡
5. ባለ 2 ሆሄ ቁጥርን በባለ አንድ ሆሄ ቁጥር ማባዛት ይቻላል፡፡

☞ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ ምረጡ፡፡

1. ከሚከተሉት ቁጥሮች ዉስጥ የ10 ብዜት የሆነዉ የቱ ነው?

   ሀ. 200 ለ.406

   ሐ. 852 መ.126

2. ከሚከተሉት ቁጥሮች ዉስጥ የ2 ብዜት የሆነዉ የቱ ነው?

   ሀ. 11 ለ.12

   ሐ. 15 መ.1

3. $8 \times 34 =$ ________

   ሀ. 42 ለ. 56

   ሐ. 252 መ. 272

4. ትክክል ያልሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ. $4 \times 10 = 40$ ለ. $30 \times 0 = 0$

ሐ. $12 \times 12 = 144$ መ. $40 \times 1 = 1$

☞ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በትዕዛዙ መሰረት መልሱ።

1. የሚከተሉትን አባዙ።

| ሀ. | ለ. | ሐ. | መ. | ሠ. | ረ. |
|---|---|---|---|---|---|
| 12 | 11 | 28 | 83 | 99 | 76 |
| ×3 | ×7 | ×5 | ×6 | ×9 | ×8 |
| = ___ | = ___ | = ___ | = ___ | = ___ | = ___ |

2. ሰንጠረዡን ሙሉ።

| × | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 9 | | | | | | | | |
| 13 | | | | | | | | |
| 34 | | | | | | | | |
| 78 | | | | | | | | |
| 97 | | | | | | | | |

3. በአንድ ቤተ-መፅሐፍት ውስጥ 4 የመፅሐፍ መደርደሪያዎች አሉ፡፡እያንዳንዳቸዉ መደርደሪያዎች 79 መጻሕፍን የመያዝ አቅም አላቸዉ፡፡በመደርደሪያዎች ላይ በአጠቃላይ ስንት መፃሕፍቶች አሉ?



# ምዕራፍ አራት

# ግማሽ እና ሩብ



*የምዕራፉ የመማር ውጤቶች፣ ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ በኋላ፡*

- *በግማሽ እና በሩብ እኩል መካፈልን ትረዳላችሁ ፡፡*
- *ግማሽን እና ሩብን በቁጥር መስመር ላይ ትገልጻላችሁ ፡፡*

## 4.1 ግማሾች

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት፡

- *እኩል መካፋፈልን መረዳት*
- *ቁሳቁሶችን በቡድን በቡድን እኩል ሁለት ቦታ መካፋፈል*
- *በየተለያዩ አገላለጽ ግማሾችን መግለጽ*

**የቡድን ስራ 4.1**



1. ተማሪዎች ለቡድናችሁ አንድ ወረቀት አዘጋጁ። የተዘጋጀዉን ወረቀት ለሁለት እኩል እጠፉት ። ከታጠፈበት ላይ በጥንቃቄ ለሁለት ቁረጡት። የተቆረጡት ወረቀቶችና መጀመሪያ ያዘጋጃችሁት ወረቀት ምን ልዩነት እንዳለዉ ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩበት።
2. ተማሪዎች አንድ ክብ የሆነ ስዕል ሳሉና በትክክል ለሁለት እኩል በእርሳስ ከፍላችሁ ግማሹን የተለየ ቀለም ቀቡት። ምን እንደ ተረዳችሁ ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩበት።


**አስተውሉ**

✍ አንድን ሙሉ ነገር ለሁለት እኩል ስንከፍል ግማሽ ይሆናል።


**ምሳሌ**

1. ግማሽን በቁሶች ስንገለጽ




<table>
<tr><td rowspan="2">ሀ</td><td></td><td></td><td></td></tr>
<tr><td>ሙሉ</td><td>ለሁለት እኩል እየተከፈለ</td><td>ግማሽ</td></tr>
<tr><td></td><td colspan="3">ከላይ የምንመለከተውን ብርቱኳን እኩል በመክፈል ግማሽን እንዴት እንደምናገኝ ነው።</td></tr>
</table>

| ለ. | ሐ |
|---|---|
|  |  |
| እኩል የተከፈሉ ፍራፍሬዎች | ከላይ የተቀቡት የተለያዩ ቅርጾች ግማሽን ያመለክታሉ፡፡ |

2. ግማሽ በቁጥር መስመር ሲገለፅ







3. የቁሶችን ስብስብ በቡድን በቡድን እኩል ሁለት ቦታ ስንከፍል

| | | |
|---|---|---|
|  |  |  |
| አንድ ስብስብ | ሁለት ስብስቦች | |

**መልመጃ 4.1**

1. በአንድ ሙሉ ስንት ግማሽ አለ?
2. የሚከተሉትን ምስሎች በማየት ግማሹን ብቻ ቀቡ፡፡

| ሀ. | ለ. | ሐ. | መ. |
|---|---|---|---|
|  |  |  |  |

## 4.2 ሩቦች

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት፡

- *ቁሶችን ደርድሮ በሩብ በሩብ መለየት*
- *ሩብን የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም መወከል*
- *የክፍል-ክፍል-ሙሉ ግንኙነቶችን ማስታወስ*

**የቡድን ስራ 4.2**



1. ተማሪዎች ለቡድናችሁ አንድ ወረቀት አዘጋጁ:: የተዘጋጀዉን ወረቀት ለሁለት እኩል እጠፉት:: የታጠፈዉን እንደገና በድጋሜ እኩል ለሁለት እጠፉት:: ከታጠፈበት ላይ በጥንቃቄ ለአራት ቁረጡት:: የተቆረጡት ወረቀቶችና መጀመሪያ ያዘጋጃችሁት ወረቀት ምን ልዩነት እንዳላቸዉ ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩበት::
2. ሩብን በቁጥር መስመር ማስቀመጥ ይቻላል? ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩበት::


**አስተዉሉ**

✍ አንድን ሙሉ ነገር ለአራት እኩል ስንከፍል ሩብ ይሆናል::



ምሳሌ

1.ቁሶችን በሩብ ስንገልፅ

ሀ. ለ.

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
|  |  |  |  |  |  |
| ሙሉ | ግማሽ | ሩብ | ሙሉ | ግማሽ | ሩብ |


2.ሩብን በማጥቆር ስንገልፅ

| | |
|---|---|
|  |  |
| የጠቆረዉ ክፍል ሩብ ነዉ | የጠቆረዉ ክፍል ሩብ ነዉ |

3.የቁሶችን ስብስብ በቡድን በቡድን እኩል አራት ቦታ ስንከፍል



| | | |
|---|---|---|
| ★★★★<br>★★★★<br>8 | ★★<br>★★<br>4 አባላት | ★★ 2 አባላት<br>★★ 2 አባላት |
| | ★★<br>★★<br>4 አባላት | ★★ 2 አባላት<br>★★ 2 አባላት |
| አንድ ሙሉ ስብስብ | ሁለት ስብስብ | አራት ስብስብ |

4.ሩብ በቁጥር መስመር ሲገለፅ



## መልመጃ 4.2

1. በአንድ ሙሉ ስንት ሩቦች አሉ?
2. ሁለት ሩቦች ስንት ግማሽ ይሆናሉ?
3. የሚከተሉትን ምስሎች ሩብን እንዲያመለክቱ አድርጋችሁ አጥቁሩ።

| | | |
|---|---|---|
|  ሀ. | ለ.  | ሐ.  |

### *የምዕራፍ አራት ማጠቃለያ*

- አንድን ሙሉ ነገር ለሁለት እኩል ስንከፍል ግማሽ ይሆናል።
- አንድን ሙሉ ነገር ለአራት እኩል ስንከፍል ሩብ ይሆናል።
- አራት ሩቦች አንድ ሙሉ ይሆናሉ።
- ስምንት ሩቦች ሁለት ሙሉ ይሆናሉ።
- አራት ግማሾች ሁለት ሙሉ ይሆናሉ።

## የምዕራፍ አራት ማጠቃለያ መልመጃ

☞ዓረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ እውነት ትክክል ካለሆነ ሀሰት በማለት መልሱ፡፡

1. ሁለት ሩቦች አንድ ግማሽ ይሆናሉ፡፡
2. አንድ ሙሉ አራት ሩቦችን ይይዛል፡፡
3. አንድን ብርትኳን ለአራት እኩል ብንከፍል ግማሽን እናገኛለን፡፡
4. ሁለት ሩቦች አራት ግማሽን ይሰጣሉ፡፡

☞ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡

1. ሁለት ግማሾች እኩል የሚሆኑት ከየትኛው ጋር ነው?

   ሀ. ሁለት ሩቦች ለ.አንድ ሙሉ

   ሐ. ሶስት ሩቦች መ. ሁለት ሙሉ

2. ስምንት ሩቦች ስንት ሙሉ ይሆናሉ?


   ሀ. 2 ለ.4 ሐ.1 መ.5

3. አንድን ሙሉ ነገር ለአራት እኩል ስንከፍል ስንት ሩቦች እናገኛለን?

   ሀ.2 ለ.4 ሐ.6 መ.5

4. የአንድ ሙሉ ነገር ግማሽ ስንት ሩቦችን ይይዛል?

   ሀ.4 ለ.6 ሐ.8 መ.2



5.  የተቀባው ምን ያህሉ ነወው?

   ሀ. ሩብ ለ. ግማሽ




   ሐ. ሁለት ሩቦች መ. ሶስት ሩቦች

☞ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በትዕዛዙ መሰረት መልሱ።


1. ግማሹን አጥቁሩ

| ሀ. | ለ. | ሐ. | መ. | ሠ. |
|---|---|---|---|---|
|  |  |  |  |  |


2. ሩቡን አጥቁሩ።

| ሀ. | ለ. | ሐ. | መ. |
|---|---|---|---|
|  |  |  |  |

3. የሚከተሉትን ቅርፆች ለሁለት እኩል በመክፈል ግማሹን አጥቁሩ።



4. የሚከተሉትን ቅርፆች ለአራት እኩል በመክፈል ሩቡን አጥቁሩ።



# ምዕራፍ አምስት

# ንድፎች

*የምዕራፉ የመማር ውጤቶች፣□□□ ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ በኋላ:*

- *የንድፎችን መደጋገም ትረዳላችሁ።*



## 5.1 አሃዳዊ ድግግሞሽ

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት:

- *በተሰጠው ንድፍ ላይ አሃዳዊ ድግግማሽን መለየት*

ተግባር 5.1

1.ቀጥሎ የተዘረዘሩትን በማየት አሃዳዊ ንድፍ የሆኑትንና አሃዳዊ ንድፍ ያልሆኑትን ለዩ።

| | |
|---|---|
| ሀ.  | ሐ.  |
| ለ.  | መ. *3 4 3 4 3 4* |
| ሠ. *1 2 1 3 2 4* | |


*2. ከላይ ያሉትን አሃዳዊ ንድፎች ባለ ስንት አሃድ እንደሆኑ ለዩ።*

## አስተዉሉ

- አሃዳዊ ንድፎች ማለት አንድ አይነት ድግግሞሽ ያላቸዉ ስዕሎች፣ቁሶች እና ቁጥሮች ማለት ነዉ።
- በአሃዳዊ ንድፎች ጊዜ አንድ ቁጥር ወይም ቁስ ብቻ ከተደጋገመ ባለ አንድ አሃድ፣ሁለት ቁጥሮች ወይም ቁሶች ብቻ ከተደጋገሙ ባለ ሁለት አሃድ፣ሶስት ቁጥሮች ወይም ቁሶች ብቻ ከተደጋገሙ ደግሞ ባለ ሶስት አሃድ እንላለን።

***ምሳሌ***

1. አሃዳዊ ድግግሞሽ በቁሶች

| *ሀ.* | *ለ* | *ሐ.* |
| --- | --- | --- |
|  |  |  |
| ባለ አንድ አሃድ | ባለ ሁለት አሃድ | ባለ ሶስት አሃድ |

2. አሃዳዊ ድግግሞሽ በቁጥሮች



ሀ. 88888 ባለ አንድ አሃድ ነው።

ለ.14 14 14 14 ባለ ሁለት አሃድ ነው።


ሐ.576 576 576 576 ባለ ሶስት አሃድ ነው።

## መልመጃ 5.1

1. አሃዳዊ ንድፍ የሆኑትን ለዩ።

| | |
|---|---|
| ሀ.  | ለ.  |
| ሐ.  | መ.78 78 78 |
| ሠ.  | ረ.657 657 657 657 |

2. ባለ ስንት አሃድ እንደሆነ ለዩ።

| | | |
|---|---|---|
| ሀ.55555 | ለ.64 64 64 64 | ሐ. 687 687 687 687 |
| መ.2341 2341 2341 2341 2341 | | ሠ.  |

3. ባለ ሁለትና ባለ ሶስት አሃድ ንድፎችን በራሳችሁ ስሩ።

## 5.2 የጎደሉ የንድፍ አባላቶች

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት፡

- *በተደጋገመ ንድፍ ላይ ያሉ የጎደሉ አባላቶችን መሙላት*
- *ንድፎችን በማስረዘም በአቅራቢያ ያሉ አባላቶችን መገመት*


**የቡድን ስራ 5.1**



1.የጎደሉ አባላቶችን አሟሉ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ሀ.  | ለ.  | ሐ.  |
| መ. 234 234 - - - | ሠ. 5972 59_2 5972 _97_ | |

2.ንድፎቹን በማየት ቀጥሎ ሊመጣ የሚችለውን ፃፉ፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ.  | ለ.  |
| ሐ. 839 839 839 __? | መ.7524 7524 7524 __? |

**ምሳሌ**




1.ለሚከተሉት ጥያቄዎች የጎደሉ አባላቶችን ሙሉ፡፡

ሀ. 18 18 _8 18 __


ለ. 134 134 1_4

ሐ. 7890 7890 7_9_ 78_ _

መ.

| | | | |
|---|---|---|---|
|  |  | ___  | ___ ___ ___ |



**መፍትሔ**

| ሀ. | ለ. | ሐ. |
|---|---|---|
| 18 18 18 18 **18** | 134 134 **134** | 7890 7890 **7890** 7890 |
| መ.  | | |

2. ድግግሞሹን በማየት ቀጥሎ ሊመጣ የሚችለውን አስቀምጡ፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ.  _ _ | ለ.  _ _ |
| ሐ. 123 123 123 _ _ _ | መ.5679 5679 5679 _ _ _ _ |

**መፍትሔ**

| | |
|---|---|
| ሀ.  | ለ.  |
| ሐ.123 123 123 **123** | መ.5679 5679 5679 **5679** |

## መልመጃ 5.2

1. የጎደሉ አባላቶችን አሟሉ።

ሀ. 84 84 84 _4 84　　　ለ.909 909 909 _ _9

ሐ. 45789 45789 45789 4_7_9 45789

2. ንድፎቹን በማየት ቀጥሎ ሊመጣ የሚችለውን ፃፉ።

ሀ.77777_ _　　　ለ.49 49 49 49 49 _ _


ሐ. 5641 5641 5641 _ _ _ _

### የምዕራፍ አምስት ማጠቃለያ



- አሃዳዊ ንድፎች ማለት አንድ አይነት ድግግሞሽ ያላቸው ቁሶች፣ስዕሎች ወይም ቁጥሮች ማለት ነው።
- በአሃዳዊ ንድፎች ጊዜ አንድ ቁጥር ወይም ቁስ ብቻ ከተደጋገመ ባለ አንድ አሃድ፣ሁለት ቁጥሮች ወይም ቁሶች ብቻ ከተደጋገሙ ባለ ሁለት አሃድ፣ሶስት ቁጥሮች ወይም ቁሶች ብቻ ከተደጋገሙ ደግሞ ባለ ሶስት አሃድ እንላለን።


## የምዕራፍ አምስት ማጠቃለያ መልመጃ


☞ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡


1. 


ቀጥሎ ሊመጣ የሚችለው የቱ ነው?

ሀ.  ለ. 

ሐ.  መ. 

2.  በባዶ ቦታው ሊገባ የሚችለው ንድፍ የቱ ነዉ?

ሀ.  ለ. 

ሐ.  መ. 

3. 6452 6452 6452 6_52 በጎደለው ቦታ ሊገባ የሚችለው ቁጥር የቱ ነው?

ሀ.2 ለ.4


ሐ.6 መ.5


4. 149 149 149 149 ቀጥሎ ሊመጣ የሚችለው ንድፍ የቱ ነው?

ሀ.149 ለ.9

ሐ.14 መ.49

☞የሚከተሉትን ጥያቄዎች በትዕዛዙ መሰረት መልሱ።


1.  የጎደለውን በመቀባት ንድፍ ስሩ።

2.  ቀጥሎ የሚመጣውን በመቀባት ንድፍ ስሩ።

3. 6856 6856 6856 6_5_ ባዶ ቦታውን በመሙላት ንድፍ ስሩ።

# ምዕራፍ ስድስት

# ልኬት፡ ርዝመት ፣ መጠነቁስ እና ይዘት



*የምዕራፉ የመማር ውጤቶች፡-ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ በኋላ፡*

- *በኢትዮጵያ ባህላዊ መለኪያ ዘዴዎች ርዝመት ፣ መጠነቁስና ይዘትን ትለካላችሁ፡፡*
- *በዘመናዊ መለኪያ ዘዴዎች ርዝመት ፣ መጠነቁስና ይዘትን ትለካላችሁ፡፡*

## 6.1. ርዝመትን በሳንቲሜትር እና በሜትር መለካት

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት፡

- *የቁሶችን ርዝመት በኢትዮጵያ ባህላዊ የመለኪያ ዘዴዎች መለካትን መረዳት*
- *የቁሶችን ርዝመት በሜ እና በሴ.ሜ መለካትን መረዳት*


## የቡድን ስራ 6.1



1. የመማሪያ ክፍላችሁን በር ርዝመት በስንዝር እየለካችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።
2. የክፍላችሁን ርዝመት በእርምጃ ለኩ።
3. የጥቁር ሰሌዳችሁን በክንድ ለኩ።
4. ከላይ የለካችኋቸዉን እንደገና በሳንቲ ሜትር እና በሜትር ለክታችሁ ተወያዩበት።

### አስተዉሉ

- እርምጃ፣ስንዝርእና ክንድ ባህላዊ የርዝመት መለኪያ ምድቦች ናቸዉ።
- ሜትርና ሳንቲ ሜትር ዘመናዊ የርዝመት መለኪያ ምድቦች ናቸዉ።
- ሳንቲ ሜትር ባጭሩ ሲፃፍ ሳ.ሜ ይሆናል።




- ሜትር ባጭሩ ሲፃፍ ሜ ይሆናል።




**ምሳሌ**

1 ባህላዊ የርዝመት መለኪያዎች

| | | | |
|---|---|---|---|
|  |  |  |  |
| ጫማ | ክንድ | ስንዝር | እርምጃ |

2.የተለያዩ ቁሶችን በሳ.ሜ ስንለካ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | 8 ሳ.ሜ እርሳስ  | 2 | 9 ሳ.ሜ ካሮት  |
| 3 |  7 ሳ.ሜ ብሎን መፍቻ | | |

## መልመጃ 6.1

1. የሒሳብ መፅሐፋችሁን በክንዳችሁ፣ በሜትርና በሳንቲ ሜትር ለኩና ፃፉ።
2. ቁመታችሁ ስንት ሜትር እና ስንት ሳንቲ ሜትር ነው?
3. የራሳችሁን እጅ በመጠቀም የሚከተሉትን በሳ.ሜ ለኩና ፃፉ።



ሀ. ትንሽ ጣት　　ለ. የቀለበት ጣት

ሐ. ረጅሙ ጣት　　መ. አዉራ ጣት

ሠ. ሌባ ጣት

4. የሚከተሉትን ቁሶች በሳ.ሜ ለኩና ፃፉ?

ሀ. 

ለ. 

ሐ. 

## 6.2 ተመሳሳይ የርዝመት መለኪያ ምድብ ያላቸውን መደመርና መቀነስ

*ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት:*

- *ተመሳሳይ የርዝመት መለኪያ ምድብ ያላቸውን መደመርና መቀነስ*

**ተግባር 6.1**

1. የተለያዩ ርዝመት ያላቸዉን ቁሶች በአንድ አይነት መለኪያ በመለካት መደመርና መቀነስ ይቻላል?
2. ባዶ ቦታዉን ሙሉ።

ሀ.5ሜ + 15ሜ=____ሜ    ለ.12 ሳ.ሜ - 8 ሳ.ሜ=___ሳ.ሜ

3. በ7 ሜትር ርዝመት ገመድ ላይ 5 ሜትር ቢጨመርላችሁ በአጠቃላይ ስንት ሜትር ርዝመት ያለው ገመድ ይሆንላችኋል?
4. 90 ሳ.ሜ ርዝመት ካለው ገመድ 30 ሳ.ሜ ርዝመት ቢቆረጥ የቀረው ምን ያህል ይሆናል?

## አስተዉሉ

- አንድ አይነት የርዝመት መለኪያ ወይም ምድብ ያላቸዉን ቁሶች መደመርና መቀነስ ይቻላል፡፡
- የተለያየ አይነት የርዝመት መለኪያ ወይም ምድብ ያላቸዉን ቁሶች መደመርና መቀነስ አይቻልም፡፡

**ምሳሌ**

1. ባዶ ቦታዉን ሙሉ፡፡

   ሀ. 25ሜ + 14ሜ=___ሜ

   ለ. 36ሳ.ሜ-22ሳሜ=____ሳ.ሜ

   ሐ. 97ሜ + 48ሜ=___ሜ

   መ.27ሳ.ሜ + 84 ሳ.ሜ=____ሳ.ሜ

**መፍትሔ**

| | |
|---|---|
| ሀ.25ሜ+14ሜ=39ሜ | ለ.36ሳ.ሜ-22ሳሜ=14ሳ.ሜ |
| ሐ.97ሜ+48ሜ=145ሜ | መ.27ሳ.ሜ+84ሳ.ሜ=111ሳ.ሜ |

2. ደራርቱ በጠዋት ተነስታ 357 ሜትር የሩጫ ልምምድ አደረገች፡፡ ሰለሞን ደግሞ 456 ሜትር የሩጫ ልምምድ አደረገ፡፡

ሀ. በአጠቃላይ ሁለቱ ምን ያህል ሜትር ልምምድ ሰሩ?

ለ. የሰለሞን ልምምድ ከደራርቱ ልምምድ በምን ያህል ሜትር ይበልጣል?

**መፍትሔ**

| ሀ. ያደረጉት ልምምድ | ለ. የሰለሞን ልምምድ-የደራርቱ ልምምድ |
|---|---|
| = የደራርቱ+ የሰለሞን | = 456ሜ - 357ሜ |
| = 357ሜ + 456ሜ | = 99ሜ ስለዚህ ሰለሞን ያደረገው |
| =813ሜ | የሩጫ |

**መልመጃ 6.2**

1. የሚከተሉትን አስሉ፡፡

ሀ. 92 ሜ + 12 ሜ=__ሜ

ለ. 27 ሜ - 15 ሜ=__ሜ

ሐ. 89 ሳ.ሜ + 19 ሳ.ሜ=__ሳ.ሜ

መ. 48 ሳ.ሜ - 26 ሳ.ሜ=__ሳ.ሜ

2. ርዝመታቸው እኩል የሆኑ 5 ጉንዳኖች ተከታትለው ይሄዳሉ፡፡እያንዳንዱ ጉንዳን ርዝመት 4ሳ.ሜ ቢሆን፣ የሁሉም ጉንዳኖች ርዝመት በአጠቃላይ ስንት ሳ.ሜ ይሆናል?




3. ፋጡማ ከአቶ ኤሊያስ ሱቅ 24 ሜትር ርዝመት ያለዉ ገመድ ገዛች::ከገዛችዉ ገመድ ላይ 6ሜትር ገመድ ቆርጣ ልብስ አሰጣችበት:: ፋጡማ ስንት ሜትር ገመድ ይቀራታል?

## 6.3. መጠነ ቁስ በኪሎ ግራም እና በግራም መለካት

*ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት:*

- *መጠነ ቁስን በኢትዮጵያ ባህላዊና ዘመናዊ የመለኪያ ዘዴዎች መለካት*

**የቡድን ስራ 6.2**



1. በአካባቢያችሁ የሚገኙትን ባህላዊ የመጠነ ቁስ መለኪያ መሳሪያዎችን በመዘርዘር ተወያዩባቸዉ::
2. በቡድን ሆ□ ናችሁ ትምህርት ቤት ዉስጥ በተዘጋጁ ሚዛኖች የተለያዩ እቃዎችን ክብደት ለኩ :: (ለምሳሌ:-የደብተሮችን፣ የእስክርቢቶዎችን፣ትን□ □ ንሽ ድንጋዮችን እና ሌሎችን) የትኞቹ ከባድ የትኞቹ ደግሞ ቀላል እንደሆኑ ለመምህራችሁ አሳዩ::
3. ወፍጮ ቤት የእህል መጠነ ቁስ በምን ይሰፈራል? በቡድን ሆናችሁ ተወያዩበት::



4. ከአንድ ኪሎግራም ጥጥ እና ከአንድ ኪሎግራም ጠጠር የቱ ይበልጣል? ተወያዩበት::

**አስተውሉ**

- የኢትዮጵያ ባህላዊ የመጠነ ቁስ መለኪያዎች ቁና፣ኩባያ እና የመሳሰሉት ናቸዉ።
- ኪሎግራምና ግራም ዘመናዊ የመጠነ ቁስ መለኪያ ምድቦች ናቸዉ።




- ኪሎግራም ባጭሩ ሲፃፍ ኪ.ግ ይሆናል።
- ግራም ባጭሩ ሲፃፍ ግ ይሆናል።




**ምሳሌ**

ባህላዊ የመጠነ ቁስ መለኪያዎች በከፊል

| | | | |
|---|---|---|---|
|  |  |  |  |
| ከእንጨት የተሰራ ገበታና ማንኪያ | ዱቄት በቁና | ሽንኩርት በቅርጫት | ባዶ ዘንቢል |

**መልመጃ 6.3**

1. የተለያዩ እቃዎችን መጠነ ቁስ እንዴት እንደሚለካ በአካባቢያችሁ በሚገኙ ሱቆች በመሄድ ወይም ወላጆቻችሁን ጠይቁና ተረዱ። የተረዳችሁትን ክፍል ዉስጥ ለመምህራችሁ አስረዱ።
2. በአካባቢያችሁ በሚገኝ የመጠነ ቁስ መለኪያ ቦታ በመሄድ የራሳችሁን መጠነ ቁስ ለክታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።
3. ከግራምና ከኪሎግራም ትልቁ የመጠነ ቁስ መለኪያ ማን ነዉ?

## 6.4 ተመሳሳይ የመጠነ ቁስ መለኪያ ምድብ ያላቸውን መደመርና መቀነስ

*ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት:*

- *ተመሳሳይ የመጠነ ቁስ መለኪያ ምድብ ያላቸዉን መደመርና መቀነስ*

**ተግባር 6.2**

ወ/ሮ አለሚቱ ወደ ማከፋፈያ በመሄድ ለፕሮግራማቸዉ የሚሆን 8ኪ.ግ ምስር፣ 45ኪ.ግ ሽንኩርት፣ 24ኪ.ግ ድንች እና 18ኪ.ግ ሩዝ ገዝተዉ ተመለሱ። ወ/ሮ አለሚቱ

ሀ. ስንት ኪሎ ግራም ምስርና ሩዝ ገዙ?

ለ.ስንት ኪሎ ግራም ሽንኩርትና ድንች ገዙ?

ሐ. ስንት ኪሎ ግራም ምስር፣ሽንኩርት፣ድንችና ሩዝ ገዙ?

መ. የገዙት ሽንኩርት ከሩዙ በስንት ኪሎግራም ይበልጣል?

**አስተውሉ**

- አንድ አይነት የመጠነ ቁስ መለኪያ ወይም ምድብ ያላቸዉን ቁሶች መደመርና መቀነስ ይቻላል።
- የተለያየ አይነት የመጠነ ቁስ መለኪያ ወይም ምድብ ያላቸዉን ቁሶች መደመርና መቀነስ አይቻልም።

**ምሳሌ**

1. የተማሪ አህመድ መጠነ ቁስ 52 ኪ.ግ ነው። የተማሪ አቤል መጠነ ቁስ ከአህመድ መጠነ ቁስ በ6ኪ.ግ ይበልጣል። የአቤል መጠነ ቁስ ስንት ነዉ?

**መፍትሔ**

የአቤል መጠነ ቁስ = የአህመድ መጠነ ቁስ+ 6 ኪ.ግ

=52 ኪ.ግ+6ኪ.ግ

=58 ኪ.ግ

2. የሚከተሉትን አስሉ፡፡

ሀ. 189 ኪ.ግ + 68 ኪ.ግ=__ኪ.ግ

ለ. 285 ግ - 100 ግ=__ግ

**መፍትሔ**

ሀ. 189 ኪ.ግ + 68 ኪ.ግ=257 ኪ.ግ

ለ. 285 ግ-100 ግ=185ግ

**መልመጃ 6.4**

1. የሚከተሉትን አስሉ

ሀ.39 ኪ.ግ + 48 ኪ.ግ =__ኪ.ግ

ለ. 979 ኪ.ግ-46 ኪ.ግ =__ኪ.ግ

ሐ. 121 ግ + 237 ግ =__ግ

መ. 182 ግ - 96 ግ =__ግ


2. የአቶ አደም መጠነ ቁሰ 89ኪ.ግ ነው፡፡ የአቶ አደም መጠነቁስ መጨመር ለጤንነታቸው ጥሩ አለመሆኑን ሀኪማቸዉ ስለመከሯቸው□ የስፖርት እንቅስቃሴ በማድረግ እና የአመጋገብ ስርዓታቸውን በማስተካከል 19ኪ.ግ ቀነሱ፡፡ አሁን የአቶ አደም መጠነ ቁስ ስንት ነዉ?
3. ተማሪዎች አካባቢያችሁ ወደ ሚገኝ አንድ ሱቅ በመሄድ ባለ ሱቁ የሚገለገልባቸውን ግራም ለብቻ እና ኪሎግራም ለብቻ ደምሩ፡፡

## 6.5 ይዘትን በሊትር እና በሚሊ ሊትር መለካት

*ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃቶች፡*

- *ይዘትን በኢትዮጵያ ባህላዊ የመለኪያ ዘዴዎች መለካት*
- *ይዘትን በሊትር እና በሚሊ ሊትር መለካት*

**የቡድን ስራ 6.3**



1. ተማሪዎች በቤታችሁ የሚገኝ የወውኃ ማጠራቀሚያ ባልዲ ወይም እንስራ ስንት ሊትር የሚይዝ ይመስላችኋል? ከባልዲ ወይም ከእንስራ ሌላ በየቤታችሁ እንደ ውሃ፣ወተት፣ዘይትና ሌሎችንም ፈሳሽ ነገሮችን በምን በምን ትለካላችሁ? ዘርዝሩ፡፡ ይዘታቸዉንም በመገመት ተወያዩባቸው፡፡
2. ከአንድ ሊትር ውኃና ከአንድ ሊትር ዘይት የቱ ይበልጣል ተወያዩበት፡፡



### አስተውሉ

- ቅል፣እንስራ እና ዋንጫ ባህላዊ የይዘት መለኪያዎች ናቸዉ፡፡
- ሊትርና ሚሊ ሊትር ዘመናዊ የይዘት መለኪያ ምድቦች ናቸዉ፡፡
- ሊትር ባጭሩ ‹‹ሊ›› ይሆናል፡፡
- ሚሊ ሊትር ባጭሩ ‹‹ሚ.ሊ›› ይሆናል፡፡



**ምሳሌ**

ባህላዊ የይዘት መለኪያዎች በከፊል

| | | |
|---|---|---|
|  |  |  |
| ዉኃ በእንስራ | ዉሃ በቅል | ዋንጫ |

### መልመጃ 6.5

1. በባህላዊ እና በዘመናዊ የይዘት መለኪያ መሳሪያዎች መካከል ያለዉን ልዩነት ፃፍ?
2. ተማሪዎች አንድ ጠርሙስ በግምት ስንት ሲኒ ዉሃ መያዝ ይችላል? ሰፍረችሁ አረጋግጡ፡፡

3. በሚሊ ሊትር የተከፋፈለ እቃ ከወላጆቻችሁ ወይም ከሰፈር ፈልጉና ውኃ በመሙላት ወደ ቡና ሲኒ ገልብጡ። የቡናው ሲኒ በስንት ሚሊ ሊትር እንደሞላ ለመምህራችሁ ተናገሩ።

## 6 ተመሳሳይ የይዘት መለኪያ ምድብ ያላቸውን መደመርና መቀነስ

- *ተመሳሳይ የይዘት መለኪያ ምድብ ያላቸውን መደመርና መቀነስ*

ተግባር 6.3

1. ተመስገንና ኢትዮጵያ አንድ ትልቅ እንስራ ውኃ መሙላት ፈለጉ። ተመስገን 15 ሊትር ውኃ ቀድቶ ጨመረ። ኢትዮጵያ ደግሞ 27 ሊትር ጨመረች እና እንስራው ሞላ።

   ሀ. ተመስገን የጨመረው ውኃ ኢትዮጵያ ከጨመረችው ውኃ በስንት ሊትር ያንሳል?

   ለ. እንስራው የመያዝ አቅሙ ስንት ሊትር ነው?

2. ሊሊና ቤተሰቦቿ ደም ለመለገስ ወደ ደም ባንክ ሄዱ። አባቷ 400ሚ.ሊ. ደም፣እናቷ 300 ሚ.ሊ. ደም እና ሊሊ ደግሞ 250 ሚ.ሊ ደም ለግሰው ተመለሱ። አጠቃላይ ሊሊና ቤተሰቦቿ ስንት ሚ.ሊ ደም ለገሱ?



## አስተውሉ

- አንድ አይነት የይዘት መለኪያ ወይም ምድብ ያላቸውን ቁሶች መደመርና መቀነስ ይቻላል፡፡
- የተለያየ አይነት የይዘት መለኪያ ወይም ምድብ ያላቸውን ቁሶች መደመርና መቀነስ አይቻልም፡፡

**ምሳሌ**

1. የሚከተሉትን አስሉ፡፡

ሀ. 569 ሊ + 232 ሊ=__

ለ. 98 ሊ - 72 ሊ=__

ሐ. 700 ሚ.ሊ - 270 ሚ.ሊ=__

መ. 842 ሚ.ሊ + 131 ሚ.ሊ=__

**መፍትሔ**

| | |
|---|---|
| ሀ. 569ሊ+232ሊ=801ሊ | ሐ.700ሚ.ሊ-270ሚ.ሊ=430ሚ.ሊ |
| ለ.98ሊ-72ሊ=26ሊ | መ.842ሚ.ሊ+131ሚ.ሊ=973ሚ.ሊ |

2. የሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች በምሳ ሰዓታቸው 25ሊትር ውኃ ለመጠጥ ተዘጋጀላቸው፡፡ ከተዘጋጀላቸው የመጠጥ ውኃ ውስጥ 19 ሊትሩን ብቻ ተጠቀሙ፡፡ስንት ሊትር ውኃ ቀራቸው?

**መፍትሔ**

የቀረው ውኃ በሊትር

=የተዘጋጀው ውኃ በሊትር - የተጠቀሙት ውኃ በሊትር

=25ሊ.-19ሊ.

=6ሊ.

**መልመጃ 6.6**

1. የሚከተሉትን አስሉ፡፡

ሀ.348 ሚ.ሊ. - 290 ሚ.ሊ.=___ሚ.ሊ.

ለ.98 ሊ. + 82 ሊ.=___ሊ.

ሐ.348 ሊ. + 238 ሊ.=____ሊ.

መ.672 ሚ.ሊ. - 428 ሚ.ሊ.=___ሚ.ሊ.

2. አንድ 800 ሊትር ውኃ መያዝ የሚችል ሮቶ መሙላት ተፈለገ፡፡በውኃ እጥረት ምክንያት 690 ሊትር ብቻ ቢጨመርበት ለመሙላት ስንት ሊትር ውኃ ያስፈልጋል?




3. አንድ የጓሮ አትክልተኛ አትክልቶቹን ለማጠጣት በቀን 274 ሊትር ውኃ ቢያስፈልገው በሁለት ቀን ስንት ሊትር ውኃ ያስፈልገዋል?



## የምዕራፍ ስድስት ማጠቃለያ

✍

| 1 | መለኪያ ምድቦች | በአጭሩ ሲፃፍ |
|---|---|---|
| 2 | ሜትር | ሜ |
| 3 | ሳንቲ ሜትር | ሳ.ሜ |
| 4 | ኪሎግራም | ኪ..ግ |
| 5 | ግራም | ግ |
| 6 | ሊትር | ሊ |
| 7 | ሚሊ ሊትር | ሚ..ሊ |

✍

| 1 | ልኬት | ባሕላዊ መለኪያዎች | ዘመናዊ መለኪያዎች |
|---|---|---|---|
| 2 | ርዝመት | ክንድ፣ስንዝር፣ ጫማ፣እርምጃ | ሜትር፣ሳንቲ ሜትር |
| 3 | መጠነ ቁ | ቁና፣ጣሳ፣ጆግ | ኪሎ ግራም፣ግራም |
| 4 | ይዘት | ዋንጫ፣ቅል፣ | ሊትር፣ሚሊ ሊትር |

✍ ባህላዊ መለኪያ ምድቦች አንፃራዊና እውነተኛ ልኬትን ሊሰጡም ላይሰጡም የሚችሉ ናቸው፡፡

✍ ዘመናዊ መለኪያ ምድቦች እውነተኛነታቸው የተረጋገጠና አለም አቀፋዊ ናቸው፡፡

## የምዕራፍ ስድስት ማጠቃለያ መልመጃ

✍ ዓረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ እውነት ትክክል ካልሆነ ሀሰት በማለት መልሱ፡፡

1. ተመሳሳይ መለኪያ ምድቦችን መደመርና መቀነስ ይቻላል፡፡
2. ፈሳሽ ነገሮችን በሜትር መለካት ይቻላል፡፡
3. 50 ኪ.ግ ጨውና 50 ኪ.ግ ስኳር እኩል ናቸዉ፡፡
4. መጠነ ቁስን በኪሎግራም መለካት ይቻላል፡፡
5. ይዘት በሊትር ይለካል፡፡

✍ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡

1. ከሚከተሉት መለኪያ ምድቦች ዉስጥ የመጠነ ቁስ መለኪያ የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. ኪ.ግ ለ. ሳ.ሜ ሐ. ሜ መ. ሚ.ሊ

2. ሮቤል ከቤቱ እስከ ት/ቤት ያለው ርቀት 100ሜ ነው፡፡ ሮቤል ደርሶ መልስ ስንት ሜትር ርቀት ይጓዛል?

   ሀ. 200 ሜትር ለ.400 ሜትር

   ሐ.300 ሜትር መ.100 ሜትር

3. ከሚከተሉት አንዱ ባህላዊ የርዝመት መለኪያ ነው፡፡

   ሀ. ቁና ለ.ኩባያ ሐ.ክንድ መ.በርሜል

4. 342 ሜ+ 564 ሜ =__?

   ሀ.600 ሜ ለ.806 ሜ

   ሐ.906 ሜ መ.900 ሜ

5. 118 ሊ - 98 ሊ=__?

ሀ.207 ሊ.. ለ.30 ሊ

ሐ.260 ሊ መ.20 ሊ

6. 92 ግ - 78 ግ=__?

ሀ. 4 ግ ለ.14 ግ

ሐ.14 ግ መ.12ግ

7. 543 ኪ.ግ+305 ኪ.ግ=__?

ሀ. 847 ኪ.ግ ለ.848 ኪ.ግ

ሐ.808 ኪ.ግ መ.400 ኪ.ግ

✍የሚከተሉትን ጥያቄዎች በትዕዛዙ መሰረት መልሱ፡፡

1. የሚከተሉትን አስሉ

ሀ. 34 ሳ.ሜ + 27 ሳ.ሜ=__?

ለ.412 ግ-202 ግ=__?

ሐ. 600 ሜ + 312 ሜ=__?

መ. 918 ሚ.ሊ - 765 ሚ.ሊ=__?

2. አቶ ሰይፉ 25 ሜትር ጥቅል ሽቦ አላቸዉ፡፡ አቶ ሰይፉ የዶሮ ቤት ለመስራት 15 ሜትር ሽቦ ተጠቅመዋል፡፡ ያልተጠቀሙት ሽቦ ስንት ሜትር ነዉ?

3. የተማሪ አፎሚያ ክብደት 43 ኪ.ግ ነው፡፡ የእህቷ ክብደት ደግሞ 29 ኪ.ግ ነው፡፡ የአፎሚያ ክብደት ከእህቷ ክብደት በስንት ይበልጣል?

# ምዕራፍ ሰባት

# መረጃ አያያዝ

*የምዕራፉ የመማር ውጤት:- ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ በኋላ:*

- *መረጃ አያያዝን ትረዳላችሁ፡፡*

## 7.1 መረጃ መሰብሰብ

*ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት:*

- *ስለራሳቸው እና በአካባቢያቸው ውስጥ በሚገኙ ነገሮች ላይ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት መረጃን መሰብሰብ፡፡*

**ተግባር 7.1**

1. ተማሪዎች ቤታችሁ ውስጥ ያሉትን የቤተሰብ አባላት መዝግቡ፡፡
2. ተማሪዎች የአዝርዕት አይነቶችን ፣የጓሮ አትክልት አይነቶችን፣የቤት ውስጥ እቃዎችን፣የእንስሳት አይነቶችን ዘርዝሩ፡፡

## ምሳሌ

1. በትምህርት ቤታችሁ ዉስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶችን መዝግቡ፡፡

**መፍትሔ**

ጠረጴዛ፣ወንበር፣ጠመኔ፣መፅሐፍ፣የመማሪያ ሰሌዳ፣ ደወል፣ ሰንደቅ አላማ፣የእጅ መታጠቢያዎች እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

2. በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ በአለም ቅርስነት የተመዘገቡ ታሪካዊ ቦታዎችን መዝግቡ፡፡

**መፍትሔ**

| | ስም | ምስል |
|---|---|---|
| 1 | አክሱም |  |
| 2 | የፋሲል ግንብ |  |
| 3 | የሃረር ጀጎል ግንብ |  |

| | | |
|---|---|---|
| 4 | የላሊበላ ዉቅር አብያተ-ክርስቲያናት |  |
| 5 | ሰሜን ተራራ ብሄራዊ ፓርክ |  |
| | እና የመሳሰሉት ናቸቸዉ፡፡ | |

## መልመጃ 7.1

1. በክፍላችሁ ዉስጥ ያሉ ቁሳቁሶችን መዝግቡ፡፡
2. የክፍል ጓደኞቻችሁን እድሜ በመጠየቅ መዝግቡ፡፡
3. የምታዉቋቸዉን የቀለማት አይነቶች በደብተራችሁ መዝግቡ፡፡

3. በኢትዮጵያ ዉስጥ ያሉ ብርቅዬ እንስሳቶችን በደብተራችሁ መዝግቡ፡፡

## 7.2 ከተሳለ ስዕል በመነሳት መረጃዎችን መመደብ

*ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት፡*

- *ከተሳለ ስዕል በመነሳት ቁሶችን በመለየት መመደብ*

**የቡድን ስራ 7.1**



1. የሚከተሉትን ምስሎች በመመልከት ጥራጥሬ፣አትክልትና ፍራፍሬ በማለት መድቧቸዉ፡፡



2. የአናፂ፣ የህክምና እና የግብርና ባለሙያዎች ስራቸዉን ለማከናወን የሚጠቀሙባቸዉን መሳሪያዎች በመዘርዘር መድቧቸዉ፡፡

**አስተዉሉ**

✍መረጃዎችን ስንመድብ ቀላሉ መንገድ በአይነታቸዉ፣ በመጠናቸዉ፣በተሰሩበት ቁስ፣በአገልግሎታቸዉ፣ በባህሪያቸዉ እና በመሳሰሉት መሆን አለበት፡፡

**ምሳሌ**

1. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ምስሎች በማየት ፈሳሽና ጠጣር በማለት መድቡ፡፡




➢ ከተዘረዘሩት ዉሰጥ ፈሳሽ የሆኑት

ወተት፣ዉኃ፣ዘይት እና ጭማቂ ናቸዉ፡፡

## መፍትሔ

➢ ከተዘረዘሩት ውስጥ ጠጣር የሆኑት


ግድግዳ፣ ድንጋይ፣ባትሪ ድንጋይ፣ጠረጴዛ፣መዶሻ፣ጠመኔ ናቸዉ።

## መልመጃ 7.2

1. የሚከተሉትን ምስሎቹ በማየት የቤት እንስሳት እና የዱር እንስሳት በማለት መድቡ።



2. የሚከተሉትን ምስሎች በማየት የጤና፣የትምህርት፣ የግንባታ መሳሪያዎች በማለት መድቡ።



## 7.3 ቁሶችን በመጠቀም መረጃዎችን ማደራጀት

*ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡*

- *የተሰበሰበውን መረጃ በሰንጠረዥ ማደራጀት*
- *በሰንጠረዥ ተደራጅቶ የጠቀመጠውን መረጃ መተርጎም*

**ተግግባር 7.2**

1. ከታች የተዘረዘሩትን ፍራፍሬ፣የቤት እንስሳት እና ጥራጥሬ በማለት ምድባቸዉን በሰንጠረዥ ፃፉ፡፡ በመቀጠልም ታሊ ማርክን በመጠቀም ተርጉሙ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ብርቱኳን | በቅሎ | መንደሪን | ፍየል |
| ዶሮ | ገብስ | አተር | ሩዝ |
| ሙዝ | ፓፓያ | ትርንጎ | አቡካዶ |
| በግ | ማንጎ | ድመት | ስንዴ |

**አስተዉሉ**

✍ ታሊ ማርክ፡- የመረጃዎችን ብዛት ቆጥረን በምልክት የምናስቀመጥበት ስልት ነው፡፡

✍ መረጃን በታሊ ማርክ ስናስቀምጥ የምንጠቀምበት ምልክት ለምሳሌ፡



**ምሳሌ**

1. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን እቃዎች ከሸክላ፣ከፕላስቲክ እና ከእንጨት የተሰሩ በማለት ምድባቸዉን በሰንጠረዥ ፃፉ። በመቀጠል ታሊ ማርክን በመጠቀም አደራጁና ተርጉሙ።


ጀበና፣እንስራ፣ አልጋ፣ጆግ፣ድስት፣ቁም ሳጥን፣ሳፋ፣ምጣድ፣ ባልዲ፣ጠረጴዛ፣ሮቶ፣ወንበር፣የከሰል ማንደጃ፣ጀሪካን፣ጣባ

**መፍትሔ**

✓ መረጃዉ በሰንጠረዥ ሲቀመጥ

| ከሸክላ የተሰሩ | ከፕላስቲክ የተሰሩ | ከእንጨት የተሰሩ |
|---|---|---|
| ጀበና | ጆግ | አልጋ |
| እንስራ | ሳፋ | ቁም ሳጥን |
| ድስት | ባልዲ | ጠረጴዛ |
| ምጣድ | ሮቶ | ወንበር |
| የከሰል ማንደጃ | ጀሪካን | |
| ጣባ | | |

✓ መረጃዉ በታሊ ማርክ ሲደራጅ

| እቃዉ የተሰራበት አይነት | ታሊ ማርክ | ብዛት |
|---|---|---|
| ከእንጨት የተሰሩ |  | 4 |
| ከሸክላ የተሰሩ |  | 6 |
| ከፕላስቲክ የተሰሩ |  | 5 |

ስለዚህ፦

✓ አራት ከእንጨት የተሰሩ እቃዎች አሉ፡፡

✓ ስድስት ከሸክላ የተሰሩ እቃዎች አሉ፡፡

✓ አምስት ከፕላስቲክ የተሰሩ እቃዎች አሉ፡፡

## መልመጃ 7.3

በክፍላችሁ ዉስጥ ያሉ ተማሪዎችን ብቻ መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ስሩ፡፡

ሀ. በክፍላችሁ ዉስጥ ያሉ ተማሪዎችን እድሜ ጠይቃችሁ መዝግቡ፡፡

ለ. የመዘገባችሁትን እድሜ ከሰባት ዓመት በታች፣ከስምንት ዓመት እስከ ዘጠኝ ዓመት እና ከአስር ዓመት በላይ በማለት መድቡ፡፡

ሐ. የመደባችሁትን መረጃ ታሊ ማርክን በመጠቀም በሰንጠረዥ አደራጁ፡፡

መ. ያደራጃችሁትን መረጃ ተርጉሙ፡፡

## የምዕራፍ ሰባት ማጠቃለያ

- መረጃዎችን ስንመድብ ቀላሉ መንገድ በአይነታቸዉ፣ በመጠናቸዉ፣በተሰሩበት ቁስ፣በአገልግሎታቸዉ፣ በባህሪያቸዉ እና በመሳሰሉት መሆን አለበት።
- ታሊ ማርክ፡- የመረጃዎችን ብዛት ቆጥረን በምልክት የምናስቀመጥበት ስልት ነው።
- የመረጃ ማደራጀት ጥቅሞች፡-
  - ✓ መረጃን በቀላሉ ለማግኘት
  - ✓ መረጃን በቀላሉ ለመረዳት
  - ✓ መረጃዉን በአጭሩ ለመፃፍ እና የመሳሰሉት ናቸዉ።

## የምዕራፍ ሰባት ማጠቃለያ መልመጃ

✍ ዓረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ እዉነት ትክክል ካልሆነ ሀሰት በማለት መልሱ።

1. መረጃን የማደራጀት አንዱ ጥቅም መረጃን በቀላሉ ለማግኘት ነዉ።
2. መረጃዎችን በመጠናቸዉ፣ በአዓነታቸዉና በባህሪያቸዉ ለይቶ ማደራጀት ጠቃሚ ነዉ።
3. መረጃዎችን ለመተርጎም በሰንጠረዥ ማደራጀት አስፈላጊ ነዉ።

✍ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በትዕዛዙ መሰረት መልሱ።

1. ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ቁጥሮች አንድ የሁለተኛ ክፍል ተማሪ በአንደኛዉ ወሰነ ትምህርት ከመቶዉ ያስመዘገባቸዉ ዉጤቶች ናቸዉ።

55፣89፣67፣94፣72፣82፣69፣63

ሀ. ዉጤቶችን ከ50 በታች፣ከ50 እስከ 64፣ከ65 እስከ 80 እና ከ81 እስከ 100 በማለት መድቡ።

ለ. የመደባችሁትን ዉጤት ታሊ ማርክን በመጠቀም በሰንጠረዥ አደራጁ።

ሐ. ያደራጃችሁትን ተርጉሙ።

2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ስሩ።

ሀ. የእንስሳት ተዋፅኦ እና የጓሮ አትክልት የሆኑትን መዝግቡ፡፡

ለ. የመዘገባችኋቸዉን መረጃዎች የእንስሳት ተዋፅኦ እና የጓሮ አትክልት በማለት መድቡ፡፡

ሐ. የተመደቡትን መረጃዎች ታሊ ማርክን በመጠቀም በሰንጠረዥ አደራጁ፡፡

መ. በሰንጠረዥ የተቀመጠዉን መረጃ ተርጉሙ፡፡

# ምዕራፍ ስምንት

# የጂኦሜትሪ ቅርፆች

*የምዕራፉ የመማር ውጤቶች፣ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ በኋላ፡-*

- *የጠለል ቅርፆችን በጎናቸዉ እና በኮርነራቸዉ ብዛት ትመድባላችሁ ፡፡*
- *ቅርፆችን በጎናቸዉና በኮርነራቸዉ ትገልጻላችሁ ፡፡*

## 8.1 የጠለል ምስሎችን በማየት መመደብ

*ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት፡*



- *የጠለል ምስሎችን በማየት መመደብ*

### *የጂኦሜትሪ ቅርፆች*

**የቡድን ስራ 8.1**





ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቅርፆች የጠለል ምስል የሆኑና ያልሆኑ በማለት መድቡ፡፡

| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
|  |  |  |  |  |  |  |  |

## ምሳሌ

ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ቅርፃች የጠለል ምስል የሆኑና ያልሆኑ በማለት መድቡ፡፡

| 1. | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
|  |  |  |  |  |  |  |  |

### መፍትሔ

የጠለል ምስል የሆኑት፡-



✓ በቁጥር 1፣5 እና 7 የተወከሉት ናቸዉ፡፡

የጠለል ምስል ያልሆኑት፡-

✓ በቁጥር 2፣3፣4፣6 እና 8 የተወከሉት ናቸዉ፡፡

### መልመጃ 8.1

የሚከተሉትን ቅርፃች በማየት የጠለል ምስል የሆኑ እና የጠለል ምስል ያልሆኑ በማለት መድቡ፡፡

| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 |
|---|---|---|---|---|---|---|
|  |  |  |  |  |  |  |

## 8.2 ቅርፆችን በጎናቸውና በኮርነራቸዉ መግለፅ

*ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃት:*


- *ቅርፆችን በጎናቸውና በኮርነራቸዉ መግለፅ*

**ተግባር 8.1**

1. በቤታችሁ ዉስጥ የሚገኙትን ባለ ሶስት ጎንና ኮረነር ቅርፆች ለይታችሁ ፃፉ፡፡
2. በትምህርት ቤታችሁ ዉስጥ የሚገኙ ባለአራት ጎንና ኮርነር ቅርፆች ዘርዝራችሁ ፃፉ፡፡

**አስተዉሉ**


- የጠለል ምስሎችን በጎናቸዉና በኮርነራቸዉ መመደብ ይቻላል፡፡
- የሚከተለዉ ምስል የጠለል ምስሎች ጎንና ኮርነር ያሳያል፡፡







✍የአንድ ጠለል ምስል የጎን ብዛትና የኮርነር ብዛት እኩል ነዉ፡፡

**ምሳሌ**

1. የሚከተሉትን ቅርፆች የጎናቸዉንና የኮርነራቸዉን ብዛት በመግለፅ መድቡ፡፡



**መፍትሔ**

| የጠለል ምስል | የጎን ብዛት | የኮርነር ብዛት | የቅርፁ ምድብ |
|---|---|---|---|
|  | 3 | 3 | ጎነ ሶስት |
|  | 4 | 4 | ጎነ አራት |
|  | 5 | 5 | ጎነ አምስት |
|  | 6 | 6 | ጎነ ስድስት |




2. በትምህርት ቤታችሁ የሚገኘዉ የእግር ኳስ ሜዳ ባለ ስንት ጎን ነዉ?

## መፍትሔ

### ባለ አራት ጎን

**መልመጃ 8.2**

1. በ “ሀ” ስር ያሉትን ቅርፆች በማየት በ “ለ” ስር ካሉት የቅርፅ ምድብ ጋር አዛምዱ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1.  | ሀ. ጎነ 3 |
| 2.  | ለ. ጎነ 7 |
| 3.  | ሐ. ጎነ 8 |
| 4.  | መ. ጎነ 4 |
| 5.  | ሠ. ጎነ 6 |

## 8.3 ተመሳሳይ ምስሎችን በመጠናቸው ማወዳደር

*ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት፡*






- *ተመሳሳይ የሆኑ የጂኦሜትሪ ምስሎችን በመጠናቸዉ ማወዳደር*

## አስተዉሉ

- ተመሳሳይ ምስሎች አንድ አይነት ቅርፅ ያላቸዉና በመጠን ሊለያዩ የሚችሉ ናቸዉ፡፡
- ተመሳሳይ ምስሎችን በመጠናቸዉ ማወዳደር ይቻላል፡፡

**ምሳሌ**

1. የሚከተሉትን ምስሎች በመጠናቸዉ አወዳድሩ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ሀ.  ለ.  | ሐ.  መ.  | ሠ.  ረ.  |


**መፍትሔ**


✓ በ ሀ የተወከለዉ ጎነ ሶስት በ ለ ከተወከለዉ ጎነ ሶስት ይበልጣል፡፡


✓ በ መ የተወከለዉ ጎነ አራት በ ሐ ከተወከለዉ ጎነ አራት ያንሳል፡፡

✓ በ ሠ የተወከለዉ ጎነ ስድስት በ ረ ከተወከለዉ ጎነ ስድስት ጋር እኩል ነዉ፡፡

2. ምስሎችን በመጠናቸዉ በማወዳደር በቅደም ተከተል ስናስቀምጥ


ሀ.  (ከትንሽ ወደ ትልቅ)

ለ.  (ከትልቅ ወደ ትንሽ)


ሐ.  (ከትንሽ ወደ ትልቅ)

## መልመጃ 8.3

1. የሚከተሉትን ምስሎች በመጠናቸዉ በማወዳደር ከትንሽ ወደ ትልቅ በቅደም ተከተል አስቀምጡ።





2. የሚከተሉትን ምስሎች በመጠናቸዉ በማወዳደር ከትልቅ ወደ ትንሽ በቅደም ተከተል አስቀምጡ።



3. የሚከተሉትን የጠለል ምስሎች መጠናቸዉን በማየት የ < ፣ > ወይም = ምልክትን በባዶ ቦታዉ በማስገባት አወዳድሩ፡፡

ሀ.  ________ 

ለ.  ________ 

ሐ.  ________ 





## 8.4 ጠጣር ምስሎችን መለየት



*ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት፡*

- *ጠጣር ምስሎችን መለየት*

**ተግባር 8.2**


ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቅርፆች የጠጣር ምስል የሆኑና ያልሆኑ በማለት ለይታችሁ መድቡ፡፡

1.  2.  3.  4.  5. 


6.  7.  8.  9. 

**ምሳሌ**

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቅርፆች የጠጣር ምስል የሆኑና ያልሆኑ በማለት ለይታችሁ መድቡ።







**መፍትሔ**

| ጠጣር ምስል የሆኑት | ጠጣር ምስል ያልሆኑት |
|---|---|
|  |  |

**መልመጃ 8.4**

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቅርፆች የጠጣር ምስል የሆኑና ያልሆኑ በማለት ለይታችሁ መድቡ።

| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
|  |  |  |  |  |  |  |  |  |

## የምዕራፍ ስምንት ማጠቃለያ

- ተመሳሳይ ምስሎች አንድ አይነት ቅርፅ ያላቸዉና በመጠን ሊለያዩ የሚችሉ ናቸዉ።
- ተመሳሳይ ምስሎችን በመጠናቸዉ ማወዳደር ይቻላል።

## የምዕራፍ ስምንት ማጠቃለያ መልመጃ

- ዓረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ እዉነት ትክክል ካልሆነ ሐሰት በማለት መልሱ።


1. የጠለል ምስሎችን በመጠናቸዉ ማወዳደር አይቻልም።
2. የጠለል ምስሎችን በጎናቸዉና በኮርነራቸዉ መመደብ እንችላለን።
3. የጠለል ምስሎችና የጠጣር ምስሎች አንድ አይነት ምስሎች ነዉ።
4. የአንድ የጠለል ምስል የጎን ብዛትና የኮርነር ብዛት እኩል ናቸዉ።

- የሚከተሉትን ጥያቄዎች በትዕዛዙ መሰረት መልሱ።


  1. የሚከተሉትን የጠለል ምስሎች የጎናቸዉንና የኮርነራቸዉን ብዛት በመግለፅ መድቧቸዉ።



2. የሚከተሉትን ቅርፆች በማየት የጠለል ምስል እና የጠጣር ምስል በማለት መድቡ።



3. የሚከተሉትን ቅርፆች በመጠናቸዉ በማወዳደር ከትልቅ ወደ ትንሽ በቅደም ተከተል አስቀምጡ።



4. የሚከተሉትን ቅርፆች በመጠናቸዉ በማወዳደር ከትንሽ ወደ ትልቅ በቅደም ተከተል አስቀምጡ።



# ምዕራፍ ዘጠኝ

# የኢትዮጵያ ገንዘብ

*የምዕራፉ የመማር ውጤት፡- ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ በኋላ፡*

- *የኢትዮጵያን ገንዘብ በመጠቀም ገንዘብን ትደምራላችሁ፤ ትቀንሳላችሁ።*

## *9.1 የኢትዮጵያን ገንዘብ በመጠቀም መደመርና መቀነስ*

*ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት፡*

- *የኢትዮጵያን ገንዘብን በመጠቀም መደመርና መቀነስ*

ተግባር 9.1

1. ተማሪዎች የምታዉቋቸዉን የብር ኖቶችና የሳንቲም ዲናሮች ፃፉ።
2. የሚከተሉትን አስሉ።

ሀ. 35 ሳንቲም + 55 ሳንቲም ለ. 45 ብር + 66 ብር

ሐ. 75 ሳንቲም - 25 ሳንቲም ሠ. 250 ብር - 95 ብር

መ. 11ብር ከ50 ሳንቲም - 9 ብር ከ40 ሳንቲም

ረ. 80 ብር ከ50ሳ ንቲም + 23 ብር ከ40 ሳንቲም

## አስተዉሉ


- ገንዘብ ማለት ሕዝቦች በመግባባት ዕቃዎችን ወይም አገልግሎትን የሚገዙበት የብር ኖቶች ወይም የሳንቲም ዲናሮች ነዉ፡፡
- እያንዳንዱ የብር ኖት በላዩ ላይ በተፃፉ አሃዝ ልክ ዋጋ አለዉ፡፡
- ማንኛዉም የመገበያያ ገንዘብ በአገሪቱ መንግስት እዉቅና (ባለቤትነት) ብቻ ታትመዉ ገበያ ላይ ይዉላሉ፡፡

ምሳሌ

1. የሚከተሉትን አስሉ፡፡

ሀ. 44 ብር+ 23 ብር=__

**መፍትሔ**



44 ብር + 23 ብር = 67 ብር

ለ. 55 ብር - 33 ብር= ____

መፍትሔ

55 ብር - 33 ብር

= 22 ብር

ሐ.55 ብር ከ50 ሳንቲም -25 ብር ከ40 ሳንቲም

መፍትሔ

ስንቀንስ ሳንቲሙን ከሳንቲም ብሩን ከብሩ ላይ ነዉ።

✓ ሳንቲምን ከ ሳንቲም ስንቀንስ

50 ሳንቲም - 40 ሳንቲም

=10 ሳንቲም

✓ ብርን ከብር ስንቀንስ

55 ብር - 25 ብር

=30 ብር

ስለዚህ 55ብር ከ50 ሳንቲም - 25 ብር ከ40 ሳንቲም

=30 ብር ከ10 ሳንቲም

መ. 65 ሳንቲም- 25 ሳንቲም=__

መፍትሔ

65 ሳንቲም - 25 ሳንቲም

=40 ሳንቲም

**መልመጃ 9.1**

የሚከተሉትን አስሉ፡፡

ሀ. 40 ብር + 60 ብር=__

ለ. 17ብር ከ20 ሳንቲም+ 68 ብር ከ70 ሳንቲም=__

ሐ. 90 ሳንቲም - 80 ሳንቲም=__

መ. 74 ብር ከ65 ሳንቲም-52 ብር ከ40 ሳንቲም=__

## 9.2 ግብይትን የሚሳይ ጭውውት

*ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት፡*

- *ግብይትን በጭዉዉት መለማማድ*

**የቡድን ስራ 9.1**



1. ተማሪዎች ቡድን መስርቱና ከቡድናችሁ አባላት ዉስጥ አንድ ወንድና አንድ ሴት በመምረጥ አንዳቸዉ እንደ ሻጭ አንዳቸዉ ደግሞ እንደ ገዥ በመሆን ከዚህ በታች ያለዉን ጭዉዉት በክፍል ዉስጥ በተግባር ያሳዩ፡፡

ገዥ፡- ባለ ሱቅ እንዴት አደርክ?

ሻጭ፡- ፈጣሪ ይመስገን ደህና ነኝ

አንቺስ እንዴት አደርሽ?

## • 9.3 የቃላት ፕሮብሌሞች

*ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት፡*

- *በዕለት ተዕለት ህይወታቸዉ ዉስጥ የኢትዮጲያን ገንዘብ በመጠቀም መደመርና መቀነስን መተግበር*

**ተግባር 9.2**

1. ብሩክ ልብስ ለመግዛት ወደ ገብያ ሄደ። በ475 ብር ሱሪ እና 425 ደግሞ ሸሚዝ ገዝቶ ወደ ቤቱ ተመለሰ። ብሩክ በአጠቃላይ ስንት ብር አወጣ?
2. ከሁሉም የብር ኖቶች አንድ አንድ በተናጠል ወስደን ብንደምራቸዉ በአጠቃላይ ስንት ብር ይሆናሉ?

**ምሳሌ**

1. ቃልኪዳን ዳቦ በ6 ብር ከ50 ሳንቲም፣ሙዝ በ70 ብር ከ25 ሳንቲም እና ብስኩት በ4 ብር ከ15 ሳንቲም ገዛች። ቃልኪዳን በአጠቃላይ ስንት ብርና ሳንቲም አወጣች?

**መፍትሔ**

| ቃልኪዳን ያወጣችዉ ብር | ቃልኪዳን ያወጣችዉ ሳንቲም |
|---|---|
| =6 ብር+70 ብር+4 ብር<br>=80 ብር | =50 ሳንቲም+25 ሳንቲም+15 ሳንቲም<br>=90 ሳንቲም |
| ስለዚህ ቃልኪዳን በአጠቃላይ 80 ብር ከ90 ሳንቲም አወጣች። | |

## 9.3 የቃላት ፕሮብሌሞች

*ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት፡*

- *በዕለት ተዕለት ህይወታቸዉ ዉስጥ የኢትዮጲያን ገንዘብ በመጠቀም መደመርና መቀነስን መተግበር*

**ተግባር 9.2**

1. ብሩክ ልብስ ለመግዛት ወደ ገበያ ሄደ። በ475 ብር ሱሪ እና 425 ደግሞ ሸሚዝ ገዝቶ ወደ ቤቱ ተመለሰ። ብሩክ በአጠቃላይ ስንት ብር አወጣ?
2. ከሁሉም የብር ኖቶች አንድ አንድ በተናጠል ወስደን ብንደምራቸዉ በአጠቃላይ ስንት ብር ይሆናሉ?

**ምሳሌ**

1. ቃልኪዳን ዳቦ በ6 ብር ከ50 ሳንቲም፣ሙዝ በ70 ብር ከ25 ሳንቲም እና ብስኩት በ4 ብር ከ15 ሳንቲም ገዛች። ቃልኪዳን በአጠቃላይ ስንት ብርና ሳንቲም አወጣች?

**መፍትሔ**

| ቃልኪዳን ያወጣችዉ ብር | ቃልኪዳን ያወጣችዉ ሳንቲም |
|---|---|
| =6 ብር+70 ብር+4 ብር<br>=80 ብር | =50 ሳንቲም+25 ሳንቲም+15 ሳንቲም<br>=90 ሳንቲም |
| ስለዚህ ቃልኪዳን በአጠቃላይ 80 ብር ከ90 ሳንቲም አወጣች። | |

2. የአንድ ሳሙና ዋጋ 27 ብር ቢሆንና አንድ ሳሙና ለመግዛት ለባለ ሱቁ 50 ብር ብትሰጡት ስንት ብር ይመልስላችኃል?

**መፍትሔ**

የሚመለስላችሁ ብር=ለባለ ሱቁ የሰጣችሁት-የሳሙናዉ ዋጋ

=50 ብር-27 ብር

=23 ብር

**መልመጃ 9.3**

1. ከሁሉም የሳንቲም ዲናሮች አንድ ብርን ሳንጨምር አንድ አንድ በተናጠል ወስደን ብንደምራቸዉ በአጠቃላይ ስንት ሳንቲም ይሆናሉ?
2. ከትልቁ የብር ኖት ላይ ትንሹን የብር ኖት ብንቀንስ ስንት ብር እናገኛለን?
3. ኤደን ከአቶ ሀሰን መደብር 1 ኪሎ ስኳር በ30 ብር፣2ኪሎ መኮረኒ 100ብር እና አንድ ፓኬት ክብሪት በ20 ብር ገዛች። ኤደን በአጠቃላይ ስንት ብር አወጣች?

## የምዕራፍ ዘጠኝ ማጠቃለያ

- ገንዘብ ማለት ሕዝቦች በመግባባት ዕቃዎችን ወይም አገልግሎትን የሚገዙበት የብር ኖቶች ወይም የሳንቲም ዲናሮች ነዉ፡፡
- እያንዳንዱ የብር ኖቶች በላያቸዉ ላይ በተፃፉ አሃዞች ልክ ዋጋ አላቸዉ፡፡
- ማንኛዉም የመገበያያ ገንዘብ በአገሪቱ መንግስት እዉቅና (ባለቤትነት) ብቻ ታትመዉ ገበያ ላይ ይዉላሉ፡፡

## የምዕራፍ ዘጠኝ ማጠቃለያ መልመጃ

✍ዓረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ እዉነት ትክክል ካልሆነ ሐሰት በማለት መልሱ፡፡

1. ከፍተኛዉ የብር ኖት 200 ብር ነው፡፡
2. የብር ኖቶችን መደመርና መቀነስ እንችላለን፡፡
3. ዝቅተኛዉ የሳንቲም ዲናር 50 ሳንቲም ነዉ፡፡
4. እያንዳንዱ የብር ኖት ላይ የብሩን መጠን ተፅፎ እናገኛለን፡፡

✍ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ ምረጡ፡፡

1. 54 ብር+ 37 ብር=__

ሀ.84 ብር ለ.81 ብር ሐ. 91ብር መ. 92ብር

2. 90 ሳንቲም + 5 ሳንቲም=__

ሀ.99 ሳንቲም ለ.95 ሳንቲም

ሐ. 85 ሳንቲም መ. 75 ሳንቲም

3. 75 ብር ከ 35 ሳንቲም + 225 ብር ከ 45 ሳንቲም=__

ሀ.190 ብር ከ70 ሳንቲም ለ.190 ብር ከ80 ሳንቲም

ሐ.300 ብር ከ70 ሳንቲም መ.300 ብር ከ80 ሳንቲም

4. 200 ብር ከ50 ሳንቲም - 150 ብር ከ30 ሳንቲም=__

ሀ. 50 ብር ከ20 ሳንቲም ለ.80 ብር ከ20 ሳንቲም

ሐ.50 ብር ከ80 ሳንቲም መ.230 ብር ከ30 ሳንቲም

5. የተማሪ ኤሊያስ እናት ከአንድ ሱቅ በ30 ብር ከ25 ሳንቲም ደብተር፣ በ5 ብር ከ10 ሳንቲም እርሳስ እና በ4 ብር ከ50 የእርሳስ መቅረጫ ገዙ፡፡ የተማሪ ኤሊያስ እናት በአጠቃላይ ስንት ብር አወጡ?

ሀ. 41 ብር ከ50 ሳንቲም ለ.34 ብር ከ80 ሳንቲም

ሐ.39 ብር ከ85 ሳንቲም መ.37 ብር ከ75 ሳንቲም

6. የነዚህ የብር ኖቶች ድምር ስንት ነዉ



ሀ. 

ለ. 

ሐ 

መ. 

✍ የሚከተሉትን ጥያቄዎች አስሉ፡፡

ሀ.213 ብር + 224 ብር=__

ለ.149 ብር - 125 ብር=__

ሐ.450 ብር ከ30 ሳንቲም+150 ብር ከ25 ሳንቲም

መ. 655 ብር ከ80 ሳንቲም-43 ብር ከ50 ሳንቲም

# ምዕራፍ አስር

# የኢትዮጵያ ጊዜ

*የኢትዮጵያ ጊዜ*

*የምዕራፉ የመማር ውጤቶች:-ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ በኋላ:*

- *ጊዜን በሙሉ ፣ በግማሽ እና በሩብ ሰዓት በሚዞርና በዲጂታል ሰዓት ትቆጥራላችሁ።*
- *የሰዓትንና የደቂቃን ግንኙነት ትገልጻላችሁ።*


## 10.1 ሰዓትን በሙሉ ፣በግማሽና በሩብ አቆጣጠር በዲጂታልና በሚዞር ሰዓት


*ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት:*

- *ጊዜን በሙሉ ፣በግማሽ እና በሩብ ሰዓት በሚዞርና በዲጂታል ሰዓት መቁጠርን መረዳት*


**ተግባር 10.1**

1. ከዚህ በታች ያሉትን የሰዓት ቆጣሪዎች በማየት ስንት ሰዓት እንደሆነ ለመምራችሁ በቃላችሁ ተናገሩ።

ሀ. 

ለ. 

2. ከዚህ በታች ያሉትን የሰዓት ቆጣሪዎች በማየት ስንት ሰዓት እንደሆነ በደብተራችሁ ፃፉ፡፡

ሀ.  ለ.  ሐ.  መ. 

## አስተዉሉ

- 15 ደቂቃን ሩብ ብለን እንጠራለን፡፡
- 30 ደቂቃን ተኩል ወይም ግማሽ ሰዓት ብለን እንጠራለን፡፡
- 45 ደቂቃን ሩብ ጉዳይ ብለን እንጠራለን፡፡
- በነዚህ አይነት የሚዞሩ ሰዓት ላይ፡



✓ አጠርና ወፈር ያለዉ አመልካች ሰዓት ቆጣሪ ነዉ፡፡

✓ ከሰዓት ቆጣሪዉ በመጠኑ ረዘም ያለዉ አመልካች ደቂቃ ቆጣሪ ነዉ፡፡

✓ ደቂቃ ቆጣሪዉ ከ12 ተነስቶ ተመልሶ 12 ሲደርስ (አንድ ሙሉ ዙር) አንድ ሰዓት ይሆናል፡፡

✓ ከ1 እስከ 12 ያሉ ቁጥሮች የ5 ደቂቃ ልዩነት አላቸዉ፡፡

✍በነዚህ አይነት የዲጂታል ሰዓት ላይ፡




- ✓ከሁለቱ ነጥቦች በስተግራ ያሉ ቁጥሮች ሰዓትን ያመለክታሉ፡፡
- ✓ከሁለቱ ነጥቦች በስተቀኝ ያሉ ቁጥሮች ደቂቃን ያመለክታሉ፡፡

**ምሳሌ፡**

ከዚህ በታች ያሉትን የሰዓት ቆጣሪዎች በማየት ስንት ሰዓት እንደሆነ አንብቡ፡፡

| ሀ. | ለ. | ሐ. | መ. |
|---|---|---|---|
|   |   |   |   |
| ሠ.  |  ረ. | ሰ.  | ሸ.  |

## መፍትሔ

| ዲጂታል ሰዓት | ሀ. ዘጠኝ ሰዓት ከሩብ | ለ. አስራ ሁለት ሰዓት ተኩል | ሐ. ለዘጠኝ ሩብ ጉዳይ | መ. ሶስት ሰዓት |
|---|---|---|---|---|
| የሚዞር ሰዓት | ሠ. አስራ ሁለት ሰዓት ከሩብ | ረ. ዘጠኝ ሰዓት ተኩል | ሰ. ሰባት ሰዓት | ሸ. ለሶስት ሩብ ጉዳይ |

## መልመጃ 10.1

1. ከዚህ በታች ያሉትን የሰዓት ቆጣሪዎች በማየት በፊደል ፃፉ፡፡

ሀ. 


ለ. 


ሐ. 

መ. 

2. በፊደል የተፃፉትን በቁጥር ፃፉ፡፡

ሀ. ሰባት ሰዓት ከሩብ

ለ. አስር ሰዓት ተኩል

ሐ. ለአስራ አንድ ሩብ ጉዳይ

መ. ሁለት ሰዓት

## 10.2 ሰዓትና ደቂቃ

*ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት:*

- *የሰዓትንና የደቂቃን ግንኙነት መግለፅ*

**የቡድን ስራ 10.1**



1.አንድ ሰዓት ስንት ደቂቃ እንደሆነ ተወያዩበት።

2. ከሰዓትና ከደቂቃ የጊዜ መለኪያዎች ማን ይበልጣል? ተወያዩበት።

3. 150 ደቂቃ ስንት ሰዓትና ደቂቃ ይሆናል?

**አስተዉሉ**

- 1 ሰዓት 60 ደቂቃ ነዉ።
- ግማሽ ሰዓት 30 ደቂቃ ነዉ።
- ሩብ ሰዓት 15 ደቂቃ ነዉ።

**ምሳሌ**

1.በደቂቃ የተሰጡትን ወደ ሰዓት ቀይሩ።

ሀ.120 ደቂቃ ለ.180 ደቂቃ

**መፍትሔ**

ሀ. 120ደቂቃ=60ደቂቃ + 60ደቂቃ

=1ሰዓት +1ሰዓት

=2ሰዓት

ለ.180 ደቂቃ=60 ደቂቃ + 60 ደቂቃ + 60 ደቂቃ

=3 ሰዓት

2. በሰዓት የተሰጡትን ወደ ደቂቃ ቀይሩ።

ሀ.4 ሰዓት ለ. 5 ሰዓት

**መፍትሔ**

ሀ.4 ሰዓት=1 ሰዓት + 1 ሰዓት + 1 ሰዓት + 1 ሰዓት

=60 ደቂቃ + 60 ደቂቃ + 60 ደቂቃ + 60 ደቂቃ

=240 ደቂቃ

ለ.5 ሰዓት=1 ሰዓት+1 ሰዓት+1 ሰዓት+ 1 ሰዓት+1 ሰዓት

=60ደቂቃ+60ደቂቃ+60ደቂቃ+60ደቂቃ+60ደቂቃ

=300 ደቂቃ

3. 75 ደቂቃን ወደ ሰዓትና ደቂቃ ቀይሩ።

**መፍትሔ**

75 ደቂቃ= 60 ደቂቃ+15 ደቂቃ

=1 ሰዓት ከ15 ደቂቃ

**መልመጃ 10.2**

1. በደቂቃ የተሰጠዉን ወደ ሰዓትና ደቂቃ ቀይሩ፡፡
   ሀ. 90 ደቂቃ　　ለ. 105 ደቂቃ
   ሐ. 210 ደቂቃ　　መ.135 ደቂቃ
2. በሰዓት እና በደቂቃ የተሰጡትን ወደ  ደቂቃ ቀይሩ፡
   ሀ. 3 ሰዓት ከ15 ደቂቃ　　ለ. 1ሰዓት ከ45 ደቂቃ
   ሐ. 5 ሰዓት ተኩል

## *10.3 የጊዜ የቃላት ፕሮብሌምዎችን መፍታት*

*ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት፡*

- *በዕለት ተዕለት ህይወታቸዉ ዉስጥ የኢትዮጲያን ጊዜ በመጠቀም መደመርና መቀነስን መተግበር*

**ተግባር 10.2**

1. ኢክራም የተሰጠችዉን የቤት ስራ በ30 ደቂቃ ሰርታ ጨረሰች፡፡አቤል ደግሞ የተሰጠዉን የቤት ስራ በ45 ደቂቃ ሰርቶ ጨረሰ፡፡
   ሀ. የቤት ስራዉን ቶሎ የጨረሰዉ ማን ነዉ?
   ለ. ሁለቱ ተማሪወች የቤት ስራቸዉን ለመጨረስ በአጠቃላይ ስንት ደቂቃ ተጠቀሙ?
   ሐ. አቤል የቤት ስራዉን ለመጨረስ የተጠቀመበት ደቂቃ አንድ ሰዓት ለመሙላት ስንት ደቂቃ ይቀረዋል?

2. ተማሪዎች ለመማር ሁለት ሰዓት ተኩል ወደ ክፍል ገብተው ለአምስት ሩብ ጉዳይ ለእረፍት ቢወጡ ስንት ሰዓትና ደቂቃ ተማሩ?

**ምሳሌ**

1. አንድ ክፍለ ጊዜ ለመማር 45 ደቂቃ ቢመደብለት ሁለት ክፍለ ጊዜ ለመማር ስንት ሰዓትና ደቂቃ ያስፈልጋል?

**መፍትሔ**

ለሁለት ክፍለ ጊዜ የተመደበው ደቂቃ=45 ደቂቃ+45 ደቂቃ

=90 ደቂቃ

=60 ደቂቃ+30 ደቂቃ

**=1 ሰዓት ከ30 ደቂቃ**

2. አንድ አውሮፕላን ከአዲስአባባ ተነስቶ ባህርዳር ለመድረስ 45 ደቂቃ ወሰደበት፡፡አውሮፕላኑ የወሰደበት ሰዓት አንድ ሰዓት ለመሙላት ስንት ደቂቃ ይቀረዋል?

**መፍትሔ**

አንድ ሰዓት ለመሙላት የቀረው ደቂቃ

= 1 ሰዓት(**60 ደቂቃ**)-45 ደቂቃ

=60 ደቂቃ-45 ደቂቃ

**=15 ደቂቃ**


**መልመጃ 10.3**

1. አቶ ዳኛቸዉ በአንድ ቀን ለ4 ሰዓት ያክል መፅሐፍ ቢያነብ በ3 ቀን ምን ያክል ሰዓት ያነባል?
2. የተማሪ ማህደር ከትምርት ቤት መዉጫ ሰዓት 9፡30 ነዉ። ቤቷ 10፡30 ብትደርስ ቤቷ ለመድረስ ስንት ደቂቃ ተጠቀመች?

## የምዕራፍ አስር ማጠቃለያ

- 15 ደቂቃን ሩብ፣30 ደቂቃን ተኩል ወይም ግማሽ ሰዓት እና 45 ደቂቃን ሩብ ጉዳይ ብለን እንጠራለን።
-  የሚዞር ሰዓት
- 

ዲጂታል ሰዓት
- 1 ሰዓት በዲጂታል እና በሚዞር ሰዓት ሲገለፅ፡






- 1 ሰዓት 60 ደቂቃ፣ግማሽ ሰዓት 30 ደቂቃ እና ሩብ ሰዓት 15 ደቂቃ ይሆናሉ።

## የምዕራፍ አስር ማጠቃለያ መልመጃ

- ዓረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ እዉነት ትክክል ካልሆነ ሐሰት በማለት መልሱ።

1. ሁለት ሰዓት 120 ደቂቃ ይሆናል።
2. 3:30 ሲነበብ ሶስት ሰዓት ተኩል ተብሎ ነዉ።
3. ሰዓትን ወደ ደቂቃ መቀየር ይቻላል።

- በ ሀ ስር ያሉትን የዲጂታል ሰዓት በ ለ ስር ካሉት የሚዞር ሰዓት ጋር እኩል የሆነዉን በመምረጥ አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1.  | ሀ.  |
| 2.  | ለ.  |
| 3.  | ሐ.  |
| 4.  | መ.  |

✍ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ ምረጡ፡፡

1. 240 ደቂቃ=__________ ሰዓት

ሀ.3 ለ.2 ሐ.4 መ.ሁለት ሰዓት ተኩል

2. ሶስት ሰዓት =__________ደቂቃ

ሀ.60 ለ.75 ሐ.180 መ.240

3. ይህ ሰዓት ቆጣሪ የትኛዉን ይወክላል?




ሀ. 9፡15 ለ.10፡15

ሐ.3፡00 መ.10፡00

✍ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

1. አስቴር 3፡15 ወደ ገበያ ሄዳ 5፡45 ተመለሰች፡፡አስቴር ስንት ሰዓት ቆይታ ወደ ቤቷ ተመለሰች?

2. ማክቤል ከምሽቱ 12 ሰዓት ጀምራ ለአንድ ሰዓት ተኩል ያክል አስተማሪ የሆነ ፊልም ብታይ ማክቤል ስንት ሰዓት ላይ ፊልሙን አይታ ትጨርሳለች?